## የመልእክተኞች ፡ ስም ፡ ዝርዝር ።

ኤፍሬም ፤
አሳብ ፤
በእውነቱ ፤
ታሪኩ ፤
ይነሱ ፤
መሣይ ፤
ዘመቻ ፡ ሙሉ ፡ ዓለም ፤
እንደልቡ ፤



## ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ፩ኛ ፡ ትርኢት ።

ኤፍሬም ፤
ሕይወቴን ፡ ጠላሁት ፥
አምላክን ፡ አማሁት ፥
የሰውን ፡ ሁናቴ ፡ አየሁት ፡ ለየሁት ።
እንደሌላው ፡ ሁሉ ፥
ሰው ፡ ነህ ፡ ብሎ ፡ ፈጥሮኝ ፡ በአሳብ ፥
ተንከራተትኩ ፤
እንጀራን ፡ ቆርሼ ፡ እበላለሁ ፡ እያልኩ ፤
ስንቱን ፡ ስዘላብድ ፡ ስንቱን ፡ ስቀባጥር ፥
የገዛ ፡ አከላቴን ፡ ስንቴ ፡ ስጠረጥር ፤
የተወሳሰበው ፡ የኔ ፡ አጉል ፡ ኑሮ ፥
ማንም ፡ አይገፋውም ፡ በሐሳብ ፡ ተነክሮ ፤
ጣል ፡ አድርጎ ፡ መተው ፡ ካልሆነ ፡ በተቀር ፥
መፍትሔ ፡ የለውም ፤
በአሳብ ፡ ተንከራታች ፡ ማንም ፡ አይወደውም ።

እኔ ፡ ላይ ፡ አደሙ ፡

ወጣት ፡ ሽማግሌው ፡ መነኩሴው ፡ መናኙ ፥
በጸሎት ፡ ነዋሪው ፡ ፈጣሪን ፡ አማኙ ፥
አካለ ፡ ስንኩሉ ፡ ደካማው ፡ ለማኙ ፤
እኔ ፡ ላይ ፡ አደሙ ፡ በመንከራተቴ ፥
ስለመነመነ ፡ የገዛ ፡ አካላቴ ።
ያለ ፡ ፍላጎቴ ፡ ተፈጠርኩኝና ፥
ኤፍሬም ፡ ተብያለሁ ፥
ስሙስ ፡ ሆነ ፡ ሌላው ፡ መቼ ፡ መርጫለሁ ?
ወላጅ ፡ ልጁን ፡ ቢክብ ፡ አይከለከልም ፤
ጥቅም ፡ ግን ፡ የለውም ፥
በስም ፡ ስላጌጠ ፡ ኑሮ ፡ አይደለም ፤

እኔ ፡ እኮ ፡ ተቸገርኩ ! !
በጣም ፡ ተበጠበጥኩ ፡
ጉዳቴን ፡ እዩልኝ ፡
ጤናዬ ፡ ታወከ ፡ ምነው ፡ ተረዱልኝ ።

ቀንም ፡ ሆነ ፡ ለሊት ፡ ከሰው ፡ የማይለይ !
በጅ ፡ የማይጨበጥ ፡ መከራን ፡ የሚያሳይ ፤
አንድ ፡ ነገር ፡ አለ፡ እኔን ፡ ያሰቀቀኝ ፡
ይህ ፡ ነው ፡ የማልለው ! በጣም ፡ ያስጨነቀኝ ።
አጊጦ ፡ ይመጣል ፡ ሁሉንም ፡ ያሳያል ፤
ሳይሠሩ ፡ ያደክማል ፤
በምኞት ፡ ያሰክራል ፤
በኔማ ፡ ቀልዶአል ፡ በነፍሴ ፡ ተጫውቶአል ።

መልካም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ከኔ ፡ አይለይም !
በምኞቴ ፡ መጠን ፡ የሚሰጠኝ ፡ ነገር ፡ ከኔ ፡
ጋር ፡ አይቆይም !
ስቃይ ፡ ያሳየኛል ፡ እንቅልፍ ፡ አላገኝም ።

ሳልተኛ ፡ በውኔ ፡ እቀሰቀሳለሁ !
እበጠበጣለሁ ! ብክንክን ፡ እላለሁ !
ዓይኖቼን ፡ ገልጬ ፡ ሁሉንም ፡ አያለሁ ፤
ከሰው ፡ ጋር ፡ ቁጭ ፡ ብዬ ፡ ወሬ ፡ አወራለሁ ፤
ሰውነቴ ፡ ሁሉ ፡ እዚያው ፡ ይሁን ? አይሁን ?
እንጃ ፡ ምን ፡ አውቃለሁ !
ሁከት ፡ ሲበዛብኝ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ እያየሁ ፡
አምላኬን ፡ እላለሁ ።
ስለጤንነቴም ፡ በጣም ፡ እሰጋለሁ ፤
    እጠራጠራለሁ ፤
ኀበዝ ፡ ምን ፡ ይሻላል ? ብክንክን ፡ ብያለሁ ።

በሕልም ፡ የማየውን ፡ በውኔ ፡ ሲመስለኝ ፡
በውኔ ፡ ያየሁት ፡ በሕልሜ ፡ ሲታየኝ ፡



የመኖሬ ፡ ትርጉም ፡ የጥርጥር ፡ ሆነ ፡
መንፈሴ ፡ ታወከ ፡ አሳቤ ፡ ባከነ ።

ችላ ፡ ልለው ፡ አልችል ፡ ይጐተጉተኛል ፡
አልጨብጠም ፡ እንጂ ፡ ሁሉም ፡ ይታየኛል ፤
በውኔ ፡ እቃገፃለሁ ፡ ብክንክን ፡ እላለሁ ፡
በምንም ፡ አላምንም ፡ እጠራጠራለሁ ።
እስከየት ፡ ያያሉ ፡ ሰዎች ፡ ዓይኖቻችሁ !
እንደኔው ፡ ከሆኑ ፡ አውጉኝ ፡ እባካችሁ ፤
የኔማ ፡ ይደንቃል ፡ ዓይኖቼን ፡ አጅቦ ፡ ሰው ፡
ነቴም ፡ ያያል ፤
መነሳት ፡ ሳያሻኝ ፡ ቁጭ ፡ ብዬ ፡ ይጓዛል ።

ምን ፡ ቀረኝ ! ምን ፡ ቀረኝ !
ተከፋፍሎ ፡ አልቆአል ፡ ሰውነቴ ፡ ሁሉ ፡
በየመስመራቸው ፡ ብዙ ፡ ይጓዛሉ ፡
አይከለከሉም ፡ የትም ፡ ይደርሳሉ ፤
ድንጋጤንና ፡ ፍርሃትን ፡ ይዘው ፡ ደግሞም ፡
    ይመጣሉ ።
እንደዚህ ፡ የሚያደረግ ፡ ምን ፡ ይሆን ፡ ልረዳው ፡
    ሳለሁ ፡ በሕይወቴ !
ባላንጣ ፡ ሆነብኝ ፡ የገዛ ፡ አከላቴ ።

አዬ !
እስኪ ፡ አረፍ ፡ ልበል ፡ ጭፍሮቼም ፡ ይድረሱ ፡
ሳይሠሩ ፡ ይሻሙኝ ፡ አንዳንዴ ፡ ይጐረሱ ።
(ይተኛል)

ጨልሞአል ፡ ብዬ ፡ ለማረፍ ፡ ስቃጣ ፤
ገና ፡ ጋደም ፡ ስል ፡ ጭኖ ፡ እየመጣ ፤
ይተናነቀኛል ፡ አቤት ፡ የኔ ፡ ጣጣ ።

ለምን ፡ ልንከራተት ፡ አልፈልግም ፡ ጥፋ ፡
የደሀ ፡ ቀለቤ ፡ አንተ ፡ ከንቱ ፡ ተስፋ ፡
ገለል ፡ በልልኝ ፡ አንዴ ፡ ላንቀላፋ ።

ስታንከራትተኝ ፡ በሕልሜም ፡ በውኔ ፡
ወይ ፡ የምድር ፡ ደስታ ፡ ጽድቅ ፡ አይሆን ፡ኩነኔ ።
የመፈጠር ፡ ውጤት ፡ የመኖር ፡ ትርጉሙ ፡
እንደዚህ ፡ ከሆነ ፤
አንጥሮ ፡ ሳይተኙ ፡ በቁም ፡ ካባነነ ።
መፈጠርን ፡ መጥላት ፡ ያስከትል ፡ የለምወይ ?
መጥላትስ ፡ መውደድስ ፡ መፍትሔው ፡ ይሆናል ፡ ወይ?

መላ ፡ ቅጡ ፡ ጠፋኝ ፡ ተወሳሰበብኝ !
ነገሬን ፡ ለመርሳት ፡ በሞከር ፡ ባሰብኝ ።

ሳልሠራ ፡ ቁጭ ፡ ብዬ ፡ ላብ ፡ እያሰመጠኝ ፡
የምሠራ ፡ ብሆን ፡ እንዴት ፡ በጨነቀኝ !

(ይነቃል)

አቤት ፡ የኔ ፡ ጌታ ፡ ለካስ ፡ ቅዠት ፡ ኖሮአል !
እየከፋ ፡ ሄደ ፡ ጨርሶ ፡ ብሶአል ፡
ይኸ ፡ መጥፎ ፡ በሽታ ፡ ኧረ ፡ ምን ፡ ይሻላል?
በሕልሜም ፡ በውኔ ፡ ድቅን ፡ እያለብኝ ፡
እዩኝ ፡ ሰው ፡ አልሆንም ፡ በሽታ ፡ ላይ ፡ ጣለኝ ፡
ምነው ! ምን ፡ አደረግሁ ? አቤቱ ፡ ገላግለኝ ።

አሳብ ፤

አይ ፡ ጉድ ! አይ ፡ ጉድ ! እጅን ፡ አለስልሶ ፡ አነጋገርን ፡ በማሳመር ፡ የማስተዛዘኛ ፡ ቃላትን ፡ ቢያዘንቡ ፡ ወይም ፡ ምላስን ፡ አሹሎ ፡ አቃቂርን ፡ ቢያወጡ ፡ ኑሮእኮ ፡ መፍትሄ ፡ ሊያገኝ ፡ አይችልም ። ኑሮእኮ ፡ በሥራ ፡ እንጂ ፡ በጩኸት ፡ አይደለም! አታስብ ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ ያለመስመሩ ፡ አትጨነቅ ፡ ማለትን ፡ እንጅ ፡ እቅድ ፡ ይነስህ ፡ ፕሮግራም ፡ አይኑርህ ፡ እጅ



ህን ፡ አለስልሰህ ፡ ተቀመጥ ፡ ሥራህ ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ እንስሳት ፡ በልማድ ፡ ይሁን ፡ ማለት ፡ አይደለም ። አስብ ፡ ማለትም ፡ አንተ ፡ እንደምትለው ፡ መጨነቅና ፡ መጠበብ ፤ ሊሆን ፡ የማይችለውን ፡ ሁሉ ፡ በይሆናል ፡ መመኘትና ፡ ተውሳክ ፡እንዲፈጠር ፡ ማድረግ ፡ አይደለም ።

ኤፍሬም ፤

እምዬ ፡ ገና ፡ የሁለት ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ሆኜ ፡ አቅፋኝ ፡ አገጭዋን ፡ ይዛ ፡ እንደተቀመጠች ፡ « ልጄ ፡ ወደፊት ፡ ቀን ፡ ታወጣልኝ ፡ ይሆናል ፤ ይህም ፡ በራሱ ፡ አሳብ ፡ ነው ፡ » ያለቸውእኮ ፡ አሳብ ፡ ዋጋ ፡ የለውምና ፡ ዋጋ ፡ በሌለው ፡ ነገር ፡ አትታመስ ፡ ስትለኝ ፡ ነበር ። እንዳለቸውም ፡ አሳብ ፡ ዋጋ ፡ አጥቶ ፡ ሲቀር ፡ ያ ፡ ከንቱ ፡ አሳብ ፡ በተራው ፡ እኔን ፡ ሲያውክ ፡ ይገኛል ። ሲያሳብደኝ ፡ ኑሮ ፡ ያለቅርስ ፡ አስቀረኝ ።

በእውነቱ ፤

እናትህ ፡ የሞተችው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ፤ ግን ፡ ባትሞት ፡ ኖሮ ፤ አንተም ፡ ሥራ ፡ ቢኖርህ ፡ እንዳለችው ፡ ቀን ፡ አታወጣላትም ፡ ነበር ?

ኤፍሬም ፤

ይህስ ፡ ራሱ ፡ አሳብ ፡ የፈጠረው ፡ የይሆናል ፡ ተስፋ ፡ አይደለምን ?

በእውነቱ ፤

አይደለም ! የናትህ ፡ ዕድሜ ፡ ሊረዝም ፡ ይችል ፡ ነበር ። በ፸፫ ፡ ዓመት ፡ የመሞት ፡ ውል ፡ ኖሮአት ፡ አይደለም ። አንተም ፡ ሥራን ፡ ላለመያዝ ፡ ያደረግኸው ፡ ውል ፡ የለም ፤ ሥራ ፡ ይዘህ ፡ ገንዘብ ፡ ማግኘት ፡ የምትችል ፡ ስለሆነ ፡ በውንም ፡ ሆነ ፡ በሕልም ፡ እን

ደዚህ ፡ በሆነልኝ ፤ እንዲህ ፡ በፈጠርኩ ፤ ሳልሠራ ፡ ቁጭ ፡ ብየ ፡ በበለጸግሁ ፡ ዓለምን ፡ በእጄ ፡ በጨበጥኩ ፡ ከሚለው ፡ ከንቱ ፡ ምኞት ፡ ጋር ፡ የሚመዛዘን ፡ አይደለም ። ቢታሰብ ፡ ሊሆን ፡ የሚችል ፡ ነገር ፡ አለ ። ፈጽሞ ፡ ሊሆን ፡ የማይችል ፡ ነገር ፡ እንዳለም ፡ ታውቃለህ ፤ ወይም ፡ ማወቅ ፡ አለብህ ።

ኤፍሬም ፤

እረ ፡ ወዲያ ! መልሶ ፡ እንድጨነቅ ፡ እንድበጠበጥ ፡ በእንቅልፍ ፡ በሽታ ፡ እንድሞት ፡ አታድርገኝ ! ውትወታው ፡ ይቆይልኝ ! ተጨንቄ ፡ ተበጥብጬ ! ወጥቶልኛል ፤
ይኸው ! ይኸው !
እዩት ፡ ድቅን ፡ አለ ! አሁንስ ፡ ሰው ፡ መስሎ ፡ ይኸው ፡ ይታየኛል !
ምን ፡ ዓይነት ፡ ፍርጃ ፡ ነው ! መጣ ፡ ይጠጋኛል !





አይዞህ !----! አይዞህ !----!

አትጫወትብኝ ፡ እባካህን ፡ ተወኝ !
ተውሳኩ ፡ በዛብኝ ፡ አቤቱ ፥ ገላግለኝ ።

ተው ! ተው !

አሳብ ፤

በመልኩ ፡ ብትይዘው ፡ ይሻልህ ፡ ነበረ ፤
ግን ፡ አይመለስም ፡ ሞኝ ፡ ካመረረ ፤
ነገርህ ፡ ያሰጋል ፡ ክፉኛ ፡ ከረረ ።
አንገትህን ፡ አንጋጥጠህ ፡ እጅህን ፡ አጣምረህ ፤
ሳትሰራ ፥ ቁጭ ፡ ብለህ ፡ በሆነ ፡ ትላለህ ።
ማማረር ፡ ሥርቶ ፡ ነው ፡ ሳይሳካ ፡ ሲቀር ፥
በልቶ ፡ ማደር ፡ የለም ፡ እጅን ፡ በማጣመር ፤

ኤፍሬም ፤

ሰዎች ፡ ተገናኝተው !
ሰው ፡ ብለው ፡ ወለዱኝ ፤
ራቆቴን ፡ ወልደው !
ራቆት ፡ አስኬዱኝ ፤
መፈተኛ ፡ ልሆን ፡ የስቃይ ፡ የችግር ፤
አላውቅህም ፡ ብላኝ ፡ ያለሁባት ፡ ምድር ፤

ይህም ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ?

ሁሉም ፡ በየተራው ፡ ይመክራል ፡ ይተቻል ፤
ዝቅ ፡ ብሎ ፡ መገኘት ፡ ለስድብ ፡ ያመቻል ።
በልዩ ፡ አስተሳሰብ ፡ በየተራው ፡ ተቸኝ ፤
አሳቤን ፡ ሰብስቤ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ የሚበጀኝ ፥
የምል ፡ አይደለሁም ።
ለዚህ ፡ አልበቃሁም ፤
ድኅነት ፡ አጥቅቶኝ ፡ ከሰው ፡ ጋር ፡ አልዋልሁም ፤
የሚጠቅመኝ ፡ ምክር ፡ ምንም ፡ አልሰማሁም ።



አስብ ፡ የሚሉኝም ፡ ከንቱ ፡ አስጨነቁኝ ፤
አታስብ ፡ የሚሉም ፡ ለጥቅም ፡ ፈለጉኝ ።

እየተንከራተትኩ ፡ በሁለት ፡ ኃይል ፡ መሀል ፥
ብክንክን ፡ ብያለሁ ፡ እምን ፡ ሥራ ፡ ልዋል ?

አባትና ፡ እናቴ ፡ በሕልም ፡ አግኝቻቸው ፤
ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ቀን ፡ ላወጣላቸው ፤
«ችግር ፡ የለምና ፡ አይዞአችሁ »፡ አልኩአቸው ።


ኋላም ፡ ብነን ፡ ብዬ ፡ አኳኋኔን ፡ አየሁ ፡
ሕልም ፡ እንደነበረም ፡ አሳምሬ ፡ ለየሁ ።

በሕልሜ ፡ አየሁት ! ምኑን ?
በወሬም ፡ ሰማሁት ! ስንቱን ?
ታከተኝ ፡ ደከመኝ ፡ ውጤቱን ፡ አጣሁት ፤ ለምን ?

« የዚህ ፡ ዓለም ፥ ነገር ፡ ወጥመዱ ፡ ብዙ ፡ ነው ፡
ጥበብ ፡ አይነስህ ፡ በዘዴ ፡ ታገለው » ፤
እያለች ፡ ስትመክረኝ ፡ አሳዛኝዋ ፡ እናቴ ፤
ገና ፡ በልጅነት ፡ ሳይጠና ፡ ጉልበቴ ፤
ጊዜው ፡ ደረሰና ፡ ትዝ ፡ ይለኝ ፡ ጀመረ ፡
ዘዴውማ ፡ ከኔ ፡ ተሰውሮ ፡ ቀረ ።

የእሳት ፡ ራት ፡ ልሁን ፡ አላስብም ፡ ቢቃኝ ፤
እንዲያው ፡ ላይሞላልኝ ፡ ተውሳኩ ፡ አጠቃኝ ።

ስንት ፡ ጊዜ ፡ በላሁ ጮማን  በያይነቱ ፤
ስንት ፡ ጊዜ ፡ ጠጣሁ ፡ ጠጅም ፡ በያይነቱ ፤
ሕልም ፡ ሆኖ  ባይቀር ፡ ሲነጋ ፡ ሌሊቱ ፡
እውነት ፡ ቢሆንልኝ ፡ የሕልሜ ፡ ደስታ !
ብበላ ፡ ብጠጣ ፡ ብደሰት ፡ አንድ ፡ አፍታ ፥
የደኃ ፡ ፍላጎት ፡ ከዚህ ፡ አይለይም ፤
ሆዱ ፡ ከሞላለት ፡ ሌላን ፡ አይመኝም ፤



ኤፍሬም ፤

አብርሮ ፡ አጤቃኝ ፡ የትም ! የትም ! የትም ፡
እናንተም ፡ ዝም ፡ ነው ፡ በቃህ ፡ አትሉትም ።



በእውነቱ ፤

የስንፍና ፡ ኑሮ ፡ ይበጠብጥሃል ፡
በጤናህ ፡ አይደለም ፡ ዕብደት ፡ ጀምሮሃል ።

አሳብማ ፡ ካንተ ፡ ሊለይ ፡ የሚችለው ፡
ነፍስህ ፡ ተለይታህ ፡ መሬት ፡ ስትገባ ፡ ነው ።

እንደኩብት ፡ በልማድ ፡ መኖር ፡ አይቻልም ፤
ኑሮም ፡ ያለአሳብ ፡ አይስተካከልም ።
ክፉን ፡ እየሠሩ ፡ አምላክ ፡ አምላክ ፡ ቢሉት ፡
ያንን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ቁርጥ ፡ አርገው ፡ ካልተውት ፡
አምላክን ፡ መሸንገል ፡ ድለላ ፡ ይሆናል ፤
መልካም ፡ ተግባር ፡ እንጂ ፡ መላስ ፡ ሙች ፡ ያድናል ?

እንደዚሁም ፡ ደግሞ ፡ እጅን ፡ አለስልሶ ፡
ከንቱ ፡ ቢጐለቱ ፡ በልቶ ፡ ማደር ፡ የለም ፤
ኑሮ ፡ ካልተሟላ ፡ ሰላም ፡ አይገኝም ።
የመንፈስ ፡ ጸጥታ ፡ ሊገኝ ፡ የሚችለው ፡
ጊዜውን ፡ በመምሰል ፡ ሠርተው ፡ ሲገኙ ፡ ነው ።
ሠርቶ ፡ እንደመሻሻል !
ሰነፍ ፡ ተጐልቶ ፡ ይመሻል ፡ ይነጋል ።

ታሪኩ ፤

ኑሮ ፡ ብልሃት ፡ እንጂ ፡ ቢታገሉት ፡ አይሆን ፤
ይልቅስ ፡ ካምላክ ፡ ጋር ፡ መጣላት ፡ እንዳይሆን ፤
በሱ ፡ ስራ ፡ ገብተን ፡ መፈትፈት ፡ ይቅርብን ።
እግዜር ፡ እርዳኝ ፡ ብሎ ፡ መለመን ፡ እያለ !
ተጨነቁ ፡ የሚል ፡ ባይበዛ ፡ ምን ፡ አለ ?
ላብ ፡ ካላሰመጠህ ፡ ገርጥተህ ፡ ካላዩህ !
ቅር ፡ ከተሰኙ ፡ እንደዚህ ፡ ከጠሉህ ፤
እጅህን ፡ ስጥና ፡ ውጤቱን ፡ ተመልከት ፡
ተቀምጠህ ፡ እያለህ ፡ በአሳብ ፡ ተንከራተት ።

ኤፍሬም ፤

ኧረ ፡ ወዲያ ፡ ይቅር ፡ ምኑ ፡ ይታተታል !
በኔ ፡ ላይ ፡ ከሆነ ፡ ሁሉም ፡ ይበረታል ።
ቅጫሙ ፡ ቅማሉ ፡ ትኋኑ ፡ ይብሳል ።

ይነሱ ፤

ጥሩ ፡ ይዘህ ፡ ነበር ፡ አሁንም ፡ አትልቀቅ ፣
ሰው ፡ መሆን ፡ ከፈለግህ ፡ ከሐሳብ ፡ ተላቀቅ ።
እንዲያው ፡ ላይሞላልህ ፤
አንስቶ ፡ አይጣልህ !
ስለራስህ ፡ ማወቅ ፡ አንተም ፡ አያቅትህ ።

መሣይ ፤

ኑሮ ፡ ብልሀት ፡ እንጂ ፡ በትግል ፡ አይሆንም ፤
ጉልበት ፡ ያለብልሃት ፡ ፍሬን ፡ አያስገኝም ።
ምንም ፡ አትጨነቅ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያውቃል ፤
ቀኑ ፡ ካልደረሰ ፡ በምኞት ፡ መች ፡ ያልቃል ።

አሳብ ፤

አንተ ፡ ከብት ፡ አይደለህ ፡ አእምሮ ፡ ያለህ ፡ ሰው !
በልተህ ፡ ለጥ ፡ እንድትል ፡ የምትመከረው ፤
የምትበላውስ ፡ ማን ፡ የሠራውን ፡ ነው ?
ስላልተግባባን ፡ ነው ፣ እኔን ፡ የጠላኸው ፣
የነመሣይ ፡ ምክር ፡ የሚያጠፉህ ፡ ነው ፤
ተግሳገል ፡ አሉህ ፡ ሊበሉህ ፡ ፈልገው ፤
አሳብ ፡ የሚባለው ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ሞረድ ፡ ነው ።

ከብቶቹን ፡ እያቸው ፡ በመኘገር ፡ ተከበው !
ስለማያስቡ ፡ ያልቃሉ ፡ ተበልተው ፤
ተግጠው ! ተግጠው ።

ኤፍሬም ፤

ይህስ ፡ እውነትህ ፡ ነው ፡ ከከብት ፡ እሻላለሁ ፤
ለጥ ፡ ብዬ ፡ አልተኛም ፡ ጥቂት ፡ አስባለሁ ፤



መሣይ ፤

ብቻ ፡ ሳትጠጣ ፡ ከንቱ ፡ ትሰክራለህ ፡
በሕልምህ ፡ ስትበላ ፡ በምራቅህ ፡ ብቻ ፡ ሆድክን ፡ ትሞ
ላለህ ፡
ወፍረህ ፡ አትታይ ፡ በውንህ ፡ አልበላህ ።

አሳብ ፤

እንዴት ፡ ይወፍራል ፡ ካልሠራ ፡ ካልበላ ?
በልቶ ፡ ማደር ፡ የትአል ፡ ቁጭ ፡ ብሎ ፡ በመላ !

ደክሞ ፡ መሥራት ፡ አለ ፡ ኑሮን ፡ ለማሻሻል ፤
እሱ ፡ ግን ፡ ቁጭ ፡ ብሎ ፡ ዪመሻል ፡ ይነጋል ፤
ተጎልቶ ፡ መላ ፡ መች ፡ ያጎለምሳል ?

ይነሱ ፤

አሳሳቹ ፡ በዛ ፡ ከሀዲው ፡ በረከተ ፣
ዳቢሎስ ፡ ይመስል ፡ ደሀን ፡ ወተወተ ።
ምነው ፡ አትተወው ፡ አሁን ፡ ይህን ፡ ደሀ !
ጭንቅ ፡ ውስጥ ፡ እየጣልክ ፡ ከሚጠማው ፡ ውሀ !
ቢሆን ፡ ብቻ ፡ ሆኖ ፡ ያንተ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡
ሲጨነቅ ፡ ይታያል ፡ ሁሉም ፡ በበኩሉ ።

ዘመቻ ፡ ሙሉ ፡ አለም ፡ !
(ተከናንቦ ፡ ተቀምጧል ፡)

መ ! ! ! ጭ ፡ ! ! !
ጭ ፡ ! ! ! ል ! ! ጥ

በእውነቱ ፤

መግባባት ፡ ይኑረን ፡ አቃቂር ፡ አይውጣ ፤
ሠርተው ፡ ያላፈሩት ፡ ከየትም ፡ አይመጣ ።
መተቻቸት ፡ ይቅር ፡ ጊዜ ፡ አይጥፋብን ፣
ለአለፈው ፡ ስናዝን ፡ መጭው ፡ አይባስብን ።
«አምላክ ፡ ባይቆጣ ፡ ድንጋይ ፡ ዳቦ ፡ ነበር !

በበቅሎ ፡ እርግጫ ፡ ሰማይ ፡ ባይባረር ! »
ከማለት ፡ እንራቅ ፡ ከጥንቱ ፡ እንቆቅልሽ ፡
አቅዶ ፡ የሠራው ፡ ሠርቶ ፡ ያመለጠው ፣ ሳይለን ፡
ምን ፡ አውቅልሽ ?

መጠንቀቅ ፡ ያሻናል ፡ ሠርተን ፡ መስተካከል ፡
የገነተረውን ፡ በጥበብ ፡ በማብሰል ።

ሰው ፡ በሠራው ፡ ጥበብ ፡ ባየር ፡ ሲንፈላሰስ ፣ አን
ጋጠ ፡ ያየዋል ፤

እግዚአብሔር ፡ የሠራው ፡ ምስጢር ፡ ይመስለዋል ።
ኧረ ፡ ለመሆኑ ! ሁሉም ፡ በየፊናው ፡ ጉም ፡ ጉም ፡
የሚለው ፣
ክብሬ ፡ አይነካ ፡ ብሎ ፡ የሚጮኸው ፤
ዘጠኝ ፡ ወር ፡ ተረግዞ ፣
የሰውን ፡ ቅርጽ ፡ ይዞ ፡ በመወለዱ ፡ ነው ?
ካባታችን ፡ አዳም ፡ በውርስ ፡ የመጣ ፡ ነው ?
ወይስ ፡ ያልታወቀ ፡ ሌላ ፡ ምስጢር ፡ አለው ?
የወል ፡ ስም ፡ መውጣቱ ፡ ትርጉሙ ፡ ምንድነው ?
አዎ ! ምናልባት !
በሥነ ፡ ፍጥረቱ ፡ ሰው ፡ በሙሉ ፡ ሰው ፡ ነው ፤
ልዩነት ፡ ያመጣው ፡ የሀሳብ ፡ ሥራ ፡ ነው ።

ታሪኩ ፤

ብዙ ፡ ዘዴ ፡ አለህ ፡ ሰውን ፡ ማታለያ !
በጅ ፡ የማይዳሰስ ፣ ከንቱ ፡ መደለያ ።
ምነው ፡ ብትተወው ፡ ንትርክ ፡ ባይበዛ !
ኑሮ ፡ አይደለል ፡ እንዲሁ ፡ በንዝነዛ ።

ኤፍሬም ፤

በኔ ፡ ላይ ፡ ተጫውቶአል ፡ አሰት ፡ አይባልም ፣
ይበጠብጠኛል ፡ እረፍት ፡ አላገኝም ።



እመንገድም ፡ ስሄድ ፡ አንጎሌን ፡ አዞሮ ፣
ልቤን ፡ ጥፍት ፡ አርጎ ፡ በሙሉ ፡ ሰውሮ ።
እንካ ፡ ቅመስ ፡ ሲለኝ ፡ እንቅፋቱ ፡ ሁሉ ፣
ልቤ ፡ ታወረ ፡ እንጂ ፡ ዓይኖቼ ፡ ያያሉ ።
እውር ፡ አልባልም ፡ አፍጥጬ ፡ እያለሁ ፣
ምን ፡ ጎደለኝ ፡ ብዬ ፡ እርዳታ ፡ አገኛለሁ ።

(ዘግየት ፡ ብሎ ) ፤

አቤት ! አሻንጉሊት ፡ የልጅ ፡ መጫወቻ ፤
እንደዘመኑ ፡ ዳንስ ፡ ማርንጌ ፡ ቻ ! ቻ ! ቻ !
የሰነፍ ፡ ተፈጥሮ ፡ እንዲያው ፡ ምኞት ፡ ብቻ ።
ዓይን ፡ አንዱጋ ፡ ሲያይ ፡ ሰውነት ፡ ሌላ ፡ ዘንድ ፡
ጠዋት ፡ ሆነ ፡ ማታ ፤
በሃሳብ ፡ መነከር ፡ ትርፉ ፡ ለበሽታ ፤
በገዛ ፡ ሥራዬ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ መገረም ፣
አይ ፡ አለመሻሻል ! አይ ፡ አለመታረም !
ለነገሩ ፡ ያህል ፡ ሁለት ፡ ዓይንን ፡ ይዘን ፣
ለሊት ፡ ተኝተንም ፡ ብዙ ፡ እናያለን ።
የባጡን ፡ የቆጡን ፡ አንዱንም ፡ ሳንይዘው ፤
የጭለማ ፡ ጉዞ ፡ ምንም ፡ ሳያግደው !
ሲመላለስ ፡ ያድራል ፡ እንቅፋትም ፡ የለው ፤
አሳብ ፡ የሚባለው ፡ የደሀ ፡ ቀለብ ፡ ነው ።

ዘመቻ ፡ ሙሉ ፡ ዓለም ፤

መ ! ! ! ! ጭ ፡ ! ! ! ጭ ፡ ! ! !

ታሪኩ ፤

ቢጨነቁ ፡ ላይሆን ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ነገር !
በምኞት ፡ ላይገኝ ፡ ሥር ፡ ቢግተረተር ፣
ቀኑ ፡ ካልደረሰ ፡ ካልበሰለ ፡ በቀር ።
ካላበጠ ፡ አይበስልም !

ካልበሰለ ፡ አይፈርጥም !
ሰዉ ፡ ቢጨነቅም ፤
ጨንገራው ፡ ቢላጥም ።
ወዲህ ፡ ቢሉት ፡ ያው ፡ ነው ፡ ወዲያ ፡ ቢሉትም ፡ ያው !
የምኞት ፡ እንጀራ ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ ጣጣው ።

በሀሳብ ፡ ያርስና ፡ ደግሞም ፡ ይዘራና ፤
መሬቱ ፡ ለስልሶ ፡ ጥሩ ፡ ያበቅልና ፤
አርሞ ፡ ኮትኩቶ ፡ አጭዶ ፡ ይወቃና ፤
ፍሬውን ፡ አይቀምስም ፡ ያልበው ፡ የነበር ፡ በሀሳብ ፡
ነውና ።
ፍሬ ፡ ሲያጣበት ፡ መልሶ ፡ ይጠምዳል ፡ በምኞት ፡
ለማረስ ፤
ለመዝራት ፡ ለማብቀል ፤ ለማጨድ ፡ ለመውቃት ፡
ለማምረት ፡ ለማፈስ ፤
ሠርተው ፡ ከሚያገኙት ፡ ደረጃ ፡ ለመድረስ ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ አይሆንም ፡ ያው ፡ አሳብ ፡ ነውና ፡
በእውነት ፡ ካላረሱ ፡ አይገኝምና ።
ጐበዝ ፡ ተው ፡ በሉልኝ ፡ ይኸ ፡ ሰው ፡ አይባክን !
በአሳብ ፡ አይጨነቅ ፡ ይለምን ፡ አምላክን ።

ኤፍሬም ፤

ችግሬ ፡ ይኸው ፡ ነው !
መፍትሔ ፡ የሌለው !
በራሴ ፡ መመራት ፡ ከቶውም ፡ አላውቀው ።
አንዱ ፡ ግራ ፡ ሲለኝ ፡ አንደኛው ፡ ወደቀኝ !
በዚህ ፡ በዚያ ፡ እያለ ፡ ሁሉም ፡ ሲጎትተኝ ፤
የምለውን ፡ አጣሁ ፡ ሁሉን ፡ እየሰማሁ ፡
መምረጥ ፡ ስላቃተኝ ፡ በመሀል ፡ ተጐዳሁ ፡
ማንንም ፡ አልወቅስም ፡ ሲፈጥረኝ ፡ ዕድሌ ፡ መሆኑን ፡
ተረዳሁ ።



አሳብ ፤

እውነትም ፡ ከብት ፡ ነህ ፡ የትም ፡ ትነዳለህ !
በተወራ ፡ ቁጥር ፡ ትለዋወጣለህ ።

መልክህ ፡ እንደሰው ፡ ነው ፡ ጠባይህ ፡ ግን ፡ እስስት ፤
ሊገባህ ፡ አይችልም ፡ ምን ፡ ያደርጋል ፡ ማተት !
ሜዳ ፡ ተሰማራ ፡ ሣር ፡ ብላ ፡ እንደከብት ።

ምነው ፡ ብታስተውል ፡ የከብቶችን ፡ ፍጥረት
ትልቁም ፡ ትንሹ !
ምንም ፡ ሳያስቡ ፡ ምግብን ፡ ብቻ ሲሹ ።

የአሳማው ፡ መፈንደቅ ፡ ለምን ፡ ይመስልሃል ?
አወፋፈሩሳ !

እየለቃቀመ ፡ ይኖራል ፡ ሳይከሳ ፡
ብዙ ፡ ሳያደክም ፡ ገንዘብ ፡ መሆኑሳ !

ኤፍሬም ፤

እኮ ! ሰውም ፡ እንደዚህ ፡ ነው ፡ ካላሰበ ፡ አይከሣ !

አሳብ ፤ የለም !!

ካልሠራ ፡ በስተቀር ፡ ለቅሞ ፡ የማይበላ ፡ መሆኑን ፡
አትርሳ !

ዘመቻ ፡ ሙሉ ፡ መ ! ! ! ጭ ! ! ! !
እ ! ! ! ል ! ! ! ም ! ! !
ለካስ ፡ ሞትም ፡ አለ ?

አሳብ ፤

ባንድ ፡ በኩል ፡ ውሻ ፡ ጌታውን ፡ የሚወድ ፤
ቢበድለው ፡ አያውቅ ፡ ሂድ ፡ ቢለው ፡ የማይሄድ ፤
በራሱ ፡ አስቦ ፡ መኖር ፡ ስለማይችል ፤
እየለቃቀመ ፡ የትም ፡ ሲዞር ፡ ቢውል !
ማታ ፡ ተመልሶ ፡ ዘበኝነት ፡ ያድራል ።

ልብ ፡ ብለህ ፡ እየው ፡ እስኪ ፡ ተመልከተው ፡
ቢበላ ፡ ባይበላ ፡ ለጌታው ፡ ታማኝ ፡ ነው ፤
ይህእኮ ፡ የሆነው ፡ ስለማያስብ ፡ ነው ።

እንደዚሁም ፡ ደግሞ ፡ ፈረሱ ፡ አህያው ፡ ግመልና ፡
በቅሎ ፡ ሁሉም ፡ ግዙፍ ፡ ሆነው !
የቀንድ ፡ ከብቶቹ ፡ ታርደው ፡ ለመበላት ፡ ሲመከር
ባቸው !
አህያው ፡ ግመሉ ፡ ተጭነው ፡ ለመሄድ ፡ ሲመጡ ፡
ተስበው !
ጉልበት ፡ ሳያንሳቸው ፡ ባያስቡእኮ ፡ ነው !
ግዙፍዋን ፡ ላም ፡ እያት ፡ ጥጃዋን ፡ እያየች ፡
ባጠባኋት ! ስትል ፥
ታልባ ፡ ታጠጣለች ፡ አንድም ፡ ነገር ፡ ሳትል ።

ግሩም ፡ ነው !

ሰነፍም ፡ ወግ ፡ አለው ፡ በታሪክ ፡ ይነሣል !
ጎበዝም ፡ ወግ ፡ አለው ፡ በታሪክ ፡ ይወሣል !
ሞኝ ፡ ሲበረክት ፡ አዋቂው ፡ ይረሣል ።

ሰማህ !

ቂል ፡ ሆነህ ፡ እንድትቀር ፡ ይሰባብኩሀል !
ጭፍራችን ፡ እያሉ ፡ አታስብ ፡ ይሉሀል !
ምነው ፡ ይግባህ ፡ እንጂ ! አምላክ ፡ የሰጠህን ፡
እንዴት ፡ ይነሱሀል ?

መድኃኒት ፡ የለውም ፡ እንዳንተ ፡ ላለ ፡ ሰው ፤
የሰውን ፡ ቅርጽ ፡ ይዞ ፡ ከከብት ፡ ያልተለየው ፡
ቢነግሩት ፡ ቢመክሩት ፡ አይሰማም ፡ ያው ፡ ያው ፡
ነው ፤
ምን ፡ ይደረግ ፡ ብሎ ፡ ጣል ፡ አርጎ ፡ መተው ፡ ነው ።



ዘመቻ ፡ ሙሉ ፡ ዓለም ፤

መ ! ! ጭ ! ! !
ጭ ! ! ! ል ! ! ጥ ! !
አይ ፡ ጉድ ፡ ለካስ ፡ ሞትም ፡ አለ ?

ኤፍሬም ፤

አሁንስ ፡ ጨነቀኝ ፡ ታዲያ ፡ የቱን ፡ ልምረጥ ?
ኧረ ፡ እስኪ ፡ ንገሩኝ !
ወይም ፡ ገለል ፡ ልበል ፡ አትሰልቹኝ ፡ ገላግሉኝ ፤
ከአቅሜ ፡ በላይ ፡ ነው ፡ ታገለው ፡ አትበሉኝ ።

ወደሉም ፡ አህያ ፡ ካንተ ፡ አላንስም ፡ ይላል ፡ እንዴት ፡
ነው ፡ ነገሩ ?
ሣር ፡ በልቶ ፡ መደሰት ፡ ምን ፡ ይሆን ፡ ሚስጢሩ ?

ሌላውም ፡ ባስተውል ፡ ቀውላላው ፡ ፈረሱ ፡ እንዲሁም ፡
ባዝራ !
እየዳኸች ፡ መጥታ ፡ «ካንተ ፡ አላንስም !» አለች ፡ እግ
ዜርን ፡ አትፈራ ።
እግዜርን ፡ አትፈራ !

እምቧ ፡ ባዮች ፡ ደግሞ ፡ እነበሬው ፡ ሁሉ ፥
ምንም ፡ አይከፉም ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ያምራሉ ፤
ሰው ፡ አስበላቸው ፡ በልተው ፡ ይኖራሉ ።

የኔ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ እየከፋ ፡ ሄዶአል ፤
ሰውነቴ ፡ ሁሉ ፡ ብክንክን ፡ ብሎአል ።
አንጎሌ ፡ ዞሮአል !

ሽማግሌን ፡ ጠርቶ ፡ ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ ጣጣ ፡ መላቀቅ ፡
ይሻላል ።

እነ ፡ አቶ ፡ ታሪኩን ፡ ሄጄ ፡ ላማክራቸው ፡
ይገላግሉኛል ፡ አዋቂዎች ፡ ናቸው ።

ሽማግሌ ፡ ይስማው ፡ ወሬውም ፡ ይዘራ !
በደሌ ፡ ይገለጽ ፡ ይታወቅ ፡ ይጣራ !

በሰው ፡ ዘንድ ፡ ይወራ ፡ ችግሬን ፡ ሰው ፡ ይየው ፡
ከተሸፋፈነ ፡ ኑሮ ፡ ምን ፡ መላ ፡ አለው ?



ምዕራፍ ፡ ፬ ።

# ሁለተኛ ፡ ትርኢት ።

እንደልቡ ፤

ለምን ፡ ጠራችሁን ፡ ኧረ ፡ እስኪ ፡ ንገሩን !
ምን ፡ አገናኛችሁ ? በሉ ፡ ግለጹልን !

ኤፍሬም ፤

ጌታዬ ! ሳላውቀው ፡ ሳያውቀኝ ፡ ልጠጋህ ፡ ይለኛል !
ጤና ፡ ይነሳኛል !
በነፍስ ፡ በሥጋዬ ፡ ይቀልድብኛል ፤
ጭፍሮቹን ፡ ሰብስቦ ፡ ይዶልትብኛል !
በሕልሜም ፡ በውኔ ፡ ምኞት ፡ ያስከረኛል ።

በውኔ ፡ የማየው ፡ ባሕሪውን ፡ ሳይለቅ !
ዓይኖቼ ፡ እያዩ ፡ ይሰውረኝና ፡ ሰውነቴን ፡ ማድቀቅ ።

በሕልም ፡ የምበላው ፡ ከቶም ፡ ላያፋፋኝ !
መጠጡ ፡ ሙብሉ ፡ ጋጋታው ፡ ገደለኝ ፤
ከእንቅልፌ ፡ ስነቃ ፡ አልለወጥም ፡ ያው ፡ ነኝ !

ሳልቀምስ ፡ እሰክራለሁ ፡ አንጎሌ ፡ ይቃገል ፡
ምን ፡ እንደማይ ፡ አላወቅ ፡ አፍጥጬ ፡ እያየሁ ፡
ታዲያ ፡ ምን ፡ ያደርጋል ፡
ምናልባት ፡ ዓይኖቼ ፡ ሰው ፡ እንዲያሰኙኝ ፡ ለጌጥ ፡
ተፈጥረዋል !
ጆሮየም ፡ ይሰማል ፡
ልቤ ፡ ተቀብሎ ፡ ከበሮን ፡ ይመታል !
ሰውነቴ ፡ ሁሉ ፡ ሲጨነቅ ፡ ይታያል ።

እግዜር ፡ ያሳያችሁ ፡ አንድ ፡ ምስኪን ፡ ደሀ ፡ ምና
ምን ፡ የሌለኝ ፡

አያገባው ፡ ገብቶ ፡ ለምን ፡ ይበጥብጠኝ ?
ወይ ፡ ሳይፈጥረኝ ፡ ብቀር ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ ባላይ !
በማይገባኝ ፡ ምስጢር ፡ እንዲህ ፡ ከምሰቃይ ።

አላስቸግራችሁ ፡ ነገሬን ፡ ላሳጥር ፡
ድሮም ፡ ለችግር ፡ ነው ፡ አምላክ ፡ ደህን ፡ መፍጠር ፤

ወይ ፡ ጉድ ! አይ ፡ ዘንድሮ !
ላቤ ፡ እንደወሀ ፡ የሚንቆረቆረው !
ፊቴ ፡ ደም ፡ የሚለብስ ፡ የሚቀያየረው !
ስሬ ፡ ተገታትሮ ፡ አጥንቴም ፡ እሚታየው !
ሊረዳኝ ፡ በማይችል ፡ ባሳብ ፡ ተይዤ ፡ ነው ።

እንደዚህ ፡ መጨነቅ ፡ እንዲህ ፡ መንገላታት ፡
ተጎሳቁሎ ፡ መኖር ፡ ባለም ፡ ለመታየት ፤
ገላጋይ ፡ ሞት ፡ ሊሆን ፡ ይግባኝ ፡ የሌለበት ።

በእውነቱ ፤
ጌትነት ፡ በምኞት ፡ የሚገኝ ፡ አይደለም ፡
ካልሠሩ ፡ በተቀር ፡ በልቶ ፡ ማደር ፡ የለም ።

አየህ !
ሳይሠሩ ፡ ጌትነት ፤
ሳይበሉ ፡ ደም ፡ ግባት ፤
እንዲገኝ ፡ መመኘት ፤
ሊያቃዠ ፡ ይችላል !
እንዳልከው ፡ ይሆናል ፤
ሥራ ፡ ፈት ፡ መሆን ፡ ለወሬ ፡ ያዝናናል ።

መሣይ ፤
የኛ ፡ ትችት ፡ ይቆይ ፡ የነሱ ፡ ይሰማ ፤
ፈርደን ፡ እንዳንገኝ ፡ ጉዳዩን ፡ ሳንሰማ ።

አቶ ፡ አሳብ ፡ መልስ ፡ ስጥ ፡ ለተነገረው ፡ ቃል ፡
በጣም ፡ አታስረዝም ፡ አጭር ፡ ቃል ፡ ይበቃል ፤



እውነት ፡ ከሆነማ ፡ ነገሩ ፡ ይደንቃል !
ሰው ፡ ክፋት ፡ ሳይኖረው ፡ ለምን ፡ ዕረፍት ፡ ያጣል ?
አንተስ ፡ የሱን ፡ ጥቃት ፡ ምን ፡ ያደርግልሃል ?

አሳብ ፤
የአምላክ ፡ ስጦታ ፡ ነው ፡ አሳብ ፡ የሚባለው ፤
ቀንም ፡ ይሁን ፡ ለሊት ፡ አብሮት ፡ የሚኖረው ፤
ሌላ ፡ መቼ ፡ ሆነ ፡ ሰው ፡ የሚያሰኘው ?

ሰው ፡ ማለት ፡ ምንድነው ፡ ካሳብ ፡ ከተለየ ?
አስቦ ፡ ካልሠራ ፡ ከአእምሮው ፡ ጋራ ፡ እየተወያየ ።

እንዳሳማ ፡ ለቅሞ ፡ በልቶ ፡ ከተኛማ !
መወለድ ፡ ብቻውን ፡ ሰው ፡ አያሰኝማ !

ይነሱ ።
ኧረ ፡ ጉደኛ ፡ ነህ ፡ በጣም ፡ ትገርማለህ !
ይህን ፡ ምስኪን ፡ ደሀ ፡ ባትጫወትበት ፡ እስኪ ፡ ምን ፡
ቸገረህ ?
አሳብ ፡ የተባልከው ፡ አንተ ፡ የማን ፡ ሰው ፡ ነህ ?

አሳብ ፤
ከሁሉም ፡ ጋር ፡ አለሁ ፡ ብቻ ፡ በመጠኑ ፡
ቁጣው ፡ ሳይረዱት ፡ ጌታዬ ፡ ምን ፡ ሆኑ !
እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ምነው ፡ ባይሰማ ?
የኋሊት ፡ መሄድ ፡ ነው ፡ ይኸ ፡ ከሆነማ ።

መሣይ ፤
ከሁሉም ፡ ጋር ፡ አለሁ !
ምን ፡ ማለትህ ፡ ይሆን ፡ ነገሩ ፡ ያሰጋል ፤
ጊዜ ፡ ፈጥሮብን ፡ ነው ፡ መቼስ ፡ ምን ፡ ይሆናል !

ለብቻው ፡ ተፈጥሮ ፡ የአዳም ፡ ልጅ ፡ በሙሉ ፡
አሁን ፡ ከአሳብ ፡ ጋር ፡ ድርብ ፡ ነው ፡ ይላሉ ።

ብዙ ፡ መስማት ፡ አለ ፡ ጊዜ ፡ ለሰጠው ፡ ሰው ፡
አታላይ ፡ ሞልቶአል ፡ አቅም ፡ ካላነሰው ።

በእውነቱ ፤

ምንም ፡ ላትግባቡ ፡ ምነው ፡ ከንቱ ፡ ልፋት !
ሰው ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ ይገባዋል ፡ መስማት ፤

ወሬ ፡ ቢደራረብ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ከሌለው ፤
ቁጭ ፡ ብሎ ፡ ማዳመጥ ፡ ጊዜን ፡ ማባከን ፡ ነው ።
ምነው ፡ ብትተዉት ፡ ጊዜን ፡ ባናጠፋ ?
ጭቅጭቅ ፡ መች ፡ ሆነ ፡ የሰው ፡ ልጆች ፡ ተስፋ !

ግራ ፡ ቀኝ ፡ ብላችሁ ፡ ሁሉንም ፡ ብታዩት ፡
አምላክ ፡ ከፈጠረው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ፍጥረት ፤
ሰውእኮ ፡ ልዩ ፡ ነው ፡ ምነው ፡ አትረዱት ?

ዘመቻ ፡ ሙሉዓለም ፤

መ ! ! !ጭ ! ! እ ! ! ል !
! ! ም ! ! ! ! ጭ ! ! ! ል !
አቤት ፡ ተነሳሁኝ ፡
ባየር ፡ ላይ ፡ ለመብረር ፡ ቲኬት ፡ አገኘሁኝ ፡
መ ! ! ጭ ! ! ል ! ! ጥ ! ! !

ይነሱ ፤

ጊዜው ፡ ተለወጠ ! እየከፋ ፡ ሄደ ፡ ጉዳዩ ፡ ያሰጋል ፤
ቁጭ ፡ ብሎ ፡ ማየት ፡ ነው ፡ ሰው ፡ እንደሆነ ፡ አብዶ
አል ፤
ሰለጠንኩ ፡ እያለ ፡ ፈጣሪውን ፡ ክዶአል ።
አርፎ ፡ እንደ ፡ መብላት ፡ ተመስገን ፡ እያለ ፡
ሰይጣን ፡ አደረበት ፡ ሁሉም ፡ ተታለለ ፤
ይህ ፡ ስምንተኛው ፡ ሺህ ፡ ክፋቱ ፡ አየለ ።

ውጥንቅጡ ፡ በዝቶ ፡ ግራ ፡ ገባን ፡ እኮ !
ቀስ ፡ በቀስ ፡ ለወጠው ፡ የፊቱን ፡ አምልኮ ፤
ግራ ፡ ቀኝ ፡ እያለ ፡ በዘዴ ፡ ሰባብኮ ።



ኤፍሬም ፤

ሁል ፡ ጊዜ ፡ ይኸው ፡ ነው ፡ እንግዲህ ፡ እወቁት ፡
ብልሃት ፡ ቢገኝልኝ ፡ እንዳልንከራተት ፡
ያለ ፡ ፍላጎቴ ፡ እንዳልወተውት ፡ ይተወኝ ፡
ለምኑት ፤
ሊጠቅመኝ ፡ አልቻለም ፡ በኃሳብ ፡ ያየሁት ፤
አላጠረቃኝም ፡ በሕልም ፡ የበላሁት ።

አሳብ ፤

አንተን ፡ የራዳሁኝ ፡ መስሎኝ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡
ምንም ፡ የለኝ ፤
ተጎልተህ ፡ ዶልት ፡ ከቶ ፡ ምን ፡ ቸገረኝ !

የማይገባው ፡ ድንጋይ ፡ ቢመክሩት ፡ ቢነግሩት !
ወደኋላ ፡ የሚል ፡ ወደፊት ፡ ሂድ ፡ ሲሉት ፡
እንዳንተ ፡ ያለው ፡ ነው ፡ የመሻሻል ፡ ጠላት ።

ካሳብ ፡ ልለይ ፡ የሚል ፡ ገራገር ፡ ደንቆሮ ፡
ይህ ፡ ቢሉት ፡ ያ ፡ ሲሉት ፡ ማይገባው ፡ ተመክሮ ፤
ባገር ፡ ውስጥ ፡ ተፈጥሮ !
የት ፡ ሊገኝ ፡ ይቻላል ፡ የመሻሻል ፡ ኑሮ ?

ያም ፡ መጥቶ ፡ ሲነግረው ፡ ጎሽ ፡ እሰይ ፡ እያለ ፤
ያንንም ፡ ሲሰማ ፡ ጉሽ ፡ እሰይ ፡ እያለ !
በራሱ ፡ የማይቆም ፡ ሲዋልል ፡ የሚኖር ፡ በቁጥር ፡
አየለ ።

በጣም ፡ የሚገርመው ፡ የሚያሳስበው ፤
አእምሮን ፡ የሚያዞር ፡ የሚያሳዝነው !

ብልሁ ፡ አዋቂው ፡ ስልጡኑ ፡ መርማሪው ፤
በልቶ ፡ ተደሳቹ ፡ ሰነፍ ፡ ጦም ፡ አዳሪው !
ዘራፊው ፡ ቀጣፊው ፡ ዓይን ፡ ባይን ፡ ነጣቂው !
ከንቱ ፡ ቁጭ ፡ ብሎ ፡ በምኞት ፡ አዳሪው ፤

ሳይለይ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ሰው ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል !
የወል ፡ ስም ፡ ነውና ፡ ዳሩ ፡ ምን ፡ ይሆናል ።

እንደዚህም ፡ አንተ ፡ ከብጤዎችህ ፡ ጋር ፡
ምንም ፡ የማይገባህ ፡ ጨርሶ ፡ ገራገር ፤
ባስረዳህ ! ብመክርህ ! አልተቀበልከኝም ፡ ስለማትረባ
እንግዲህ ፡ ሰለቸኝ ፡ ይኸው ፡ ገደል ፡ ግባ !

ታሪኩ ፤

ምነው ፡ አቶ ፡ አሳብ ፡ ነገርህ ፡ ከረረ ፡ አስተያየት ፡
አጣ !

አሳብ ፤

ምን ! ይኸው ፡ ውሎ ፡ አድሮ ፡ ከበድ ፡ ያለው ፡ መጣ !

ይነሱ ፤

ምን ፡ ዓይነት ፡ ድፍረት ፡ ነው ፡ ይኸ ፡ ሁሉ ?
ስድብ ፡ ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ቁጣ !
መጥፎ ፡ ዛር ፡ ይመስል ፡ አልላቀቅ ፡ ብለህ ፡
ራስህ ፡ ተሳስተህ ፡ ሰውን ፡ ትጎዳለህ ፡ ገደል ፡ ታገባለህ፤
አስበህ ፡ አስተውለህ ፡ አውጥተህ ፡ አውርደህ ፡
አንተ ፡ ምን ፡ አገኘህ ?

ሰነፉ ፡ አታስብ ፡ ተኛልኝ ፡ የሚለው ፡
አንተም ፡ በበኩልህ ፡ የምታቃጥለው ፤
በከንቱ ፡ አይደለም ፡ ላንድ ፡ ነገርህ ፡ ነው ።
ይኸ ፡ ሰው ፡ ምን ፡ ይሁን ? የዚህም ፡ ዓለም ፡
ነገር ፡ ፈላጊው ፡ ብዙ ፡ ነው ።

አሁን ፡ ተመልከተው ፡ ስንት ፡ ዓመት ፡ አልፎታል ፤
በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ካሳብ ፡ ጋር ፡ ኖሮአል ፤
በሕልም ፡ ይሁን ፡ እንጂ !
ለብሷል ፡ አጊጦአል ፡ ወፍሮም ፡ ታይቶአል ፤
ብንን ፡ ሲል ፡ ያው ፡ ነው ፡ ሙቼ ፡ ለውጦአል !



አሁን ፡ ልገላገል ፡ ብሎ ፡ ሲለምንህ ፤
ስንቱን ፡ ያልሆነውን ፡ ትደረድራለህ ?

ለጥቅም ፡ ከሆነ ፡ ለሱም ፡ አስብለት ፡
እንዳሻው ፡ ይጎልት ፤
አይብላ ፡ ይመንምን ፡ አይልበስ ፡ ይራቆት !
ጨርሶ ፡ አይሥራ ፡ ወሬውን ፡ ይዶልት ፤
ለመኖር ፡ ከቻለ ፡ በራሱ ፡ ፍላጎት ፤
ቅማሉ ፡ ትኋኑ ፡ ምግምግ ፡ አርገው ፡ ይበሉት !

በእውነቱ ፤

አዬ ! አለማወቅ ፡ አለመመራመር ፤
አይ ፡ ጉድ ! አለመብሰል ፡ ሞኝ ፡ መሆን ፡ ገራገር ፤

ወሬ ፡ ከተባለ ፡ ሁሉም ፡ ይደመጣል !
ሰነፍ ፡ አርም ፡ ሲሉት ፡ ሲመክሩት ፡ ይቆጣል ፤
አዋቂ ፡ ነህ ፡ ብለው ፡ ቢክቡት ፡ ይመርጣል ፤
የሰው ፡ አስተሳሰብ ፡ ይገርማል ፡ ይደንቃል ።

የዱር ፡ አራዊት !
ላላምድህ ፡ ቢሉት !
እየለቃቀሙ ፡ ቢያባብሉት !
ያሳዩትን ፡ ይሠራል ፤
ፊትን ፡ አይቶ ፡ ይመራል ፤

ስማችሁ !

ደግ ፡ ሳይታወቅ ፡ ዘላለም ፡ ይኖራል ፤
በሳቅ ፡ በጨዋታ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ይቀራል ።
የሰነፍም ፡ ወሬ ፡ ጊዜን ፡ ያባክናል ፤
የናንተ ፡ ክርክር ፡ ላዋቂ ፡ ይደንቃል ፡ እጅግ ፡ ያሳዝ
ናል ።

ሕፃንን ፡ መደለል ፡ በቀላሉ ፡ ሲቻል ፤
በስኳር ፡ በዳቦ ፡ ወይም ፡ በቁጣ ፡ ቃል ፤
ቁጣን ፡ ለማይወደው !
በዕድሜ ፡ ከፍ ፡ ላለው ፡
በስኳር ፡ በዳቦ ፡ የማይደለለው ?
አልመች ፡ የሚለው ፡ የአዋቂ ፡ ሕፃን ፡ ነው ።
እንግዲህ ፡ ይኸ ፡ ሰው ፡ ብልሃቱ ፡ ምንድር ፡ ነው ?
ሊገለል ፡ አይችልም ፡ ቁጥሩ ፡ ከሰው ፡ ጋር ፡ ነው ።

ሰማችሁ !

በድን ፡ ሆኖ ፡ መኖር ፡ ይጠቅም ፡ መስሎአችሁ ፡
ያለ ፡ አሳብ ፡ መኖር ፡ እንዴት ፡ መረጣችሁ ?
ለዚህ ፡ ዓለም ፡ ኑሮ ፡ ወሰን ፡ ሲበጅለት ፤
ምድር ፡ ላይ ፡ ሲስፋፉ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ፍጥረት ፤
የማሰብ ፡ ችሎታ ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ተሰጠ ፤
ውለታው ፡ ቀረና ፡ አላስብም ፡ የሚል ፡ ካሳቢው ፡
በለጠ ፤
የስሜቱን ፡ ትቶ ፡ ጊዜውን ፡ ለመምሰል ፡ ይህንን ፡
መረጠ ።

ግን ፡ እኮ ፡ ሰውማ !
ኧረ ፡ ቢገባውማ !
ሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ እንዲመራመር ፡ ነው ፤
ተሻሽሎ ፡ መገኘት ፡ የመኖር ፡ ትርጉም ፡ ነው ።
ሳይሻል ፡ ቢቀር ፡ እዳው ፡ የራሱ ፡ ነው ።
መጠየቅ ፡ ያሻዋል ፡ አውቆ ፡ የማይሠራ ፤
የሜዳ ፡ ጎርፍ ፡ መስሎ ፡ የትም ፡ ከሚመራ ።

እንደልቡ ፤

ካሳብ ፡ ካልተደረበን ፡ መኖር ፡ አንችልም ፡
ብለህ ፡ ስታወራ !
ካፈር ፡ የሠራህን ፡ አምላክን ፡ አትፍራ !



እግዚአብሔር ፡ መሆኑን ፡ የሚያስብልህ ፡
ስሉሱ ፡ ርቆህ ፡ ሳትረዳው ፡ ቀርተህ ፤
ይህ ፡ ቢሆን ፡ ያ ! እያልክ ፡ ታሳስተናለህ ።
ሰይጣን ፡ አንተን ፡ መስሎ ፡ ሔዋንን ፡ ሲያስት !
ይህንን ፡ ከበላሽ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትልቅ ፡
ትሆኛለሽ ፡ ብሏት ፤
አትንኪ ፡ ያላትን ፡ ሄዳ ፡ በላችና ፥
እንደምታዩት ፡ ነው ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ፈተና ።
ምን ፡ አለ ፡ ጊዜው ፡ ነው ፡ ጨርሰህ ፡ አጥፋና !

በእውነቱ ፤

ሔዋንን ፡ ያሳተ ፡ አለማሰቧ ፡ ነው ፡ ሌላ ፡ መቼ ፡ ሆነ !
እርግጥ ፡ በውጤቱ ፡ ሰዉ ፡ ተኰነነ ።
ባለማሰብዋ ፡ ነው ፡ ብትሆን ፡ ገራገር ፤
አስባ ፡ ብትሠራ ፡ አትሞኝም ፡ ነበር ።
የዚሁ ፡ ብጤ ፡ ነው ፡ አሁን ፡ ያደከመን ፥
ተመልሰን ፡ ያው ፡ ነን ፡ እንደሔዋን ፡ ዘመን ።

ዘመቻ ፡ ሙሉ ፡ ዓለም !

! ! ! ! ! ጭልጥ ! ! ! እ ! ! ል፡ም!
ይኸው ፡ ተነሳሁኝ !
ባየር ፡ ላይ ፡ ለመብረር ፡ ቲኬት ፡ አገኘሁኝ ።
የምታየው ፡ ነገር ፡ በሕይወትህ ፡ ሙሉ ፥
አዝርዕቱ ፡ አትክልቱ ፡ ሣርና ፡ ቅጠሉ ።
ሁሉም ፡ በየመልኩ ፡ እንደየጠባዩ ፥
ባሕር ፡ ውቅያኖሱ ፡ መሬቱ ፡ ድንጋዩ ፤
የቤት ፡ እንስሳቱ ፡ የዱር ፡ አራዊቱ ፥
ትላትሉ ፡ ሁሉ ፡ በራሪ ፡ አዕዋፋቱ ፥
ዝንቡ ፡ ሸረሪቱ ፡ ሁሉም ፡ በያይነቱ ፥
ቁንጫው ፡ ትኋኑ ፡ መዥገሩ ፡ ቅማሉ ፥
ትንኙ ፡ ቅጫሙ ፡ ተባዮች ፡ በሙሉ ፥

ሌላም ፡ እንደዚሁ ፡ የማናውቀው ፡ ሁሉ ፣
በድምር ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ምድርን ፡ ያጌጣሉ ፤
ጥቂት ፡ ይኖሩና ፡ ጠፍተው ፡ ይቀራሉ ።

ለዚህ ፡ አጭር ፡ ኑሮ ፡ መጭ ፡ ይላል ፡ አሳቤ !
ሞት ፡ እንደሆነ ፡ አይቀር ፡ ተሞልቷል ፡ መዝገቤ ።

እንደልቡ !

አይ ፡ ጥጋብ !
አይ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አለማመስገን ፣ አሁን ፡ ምን ፡
ጎደለበት ፡ ብለህ ፡ ነው ? ኧረ ፡ ተው ! ኧረ ፡ ተው ፣
በእናንተ ፡ ምክንያት ፡ አንድ ፡ ቁጣ ፡ አይላክብን ፣
ኧረ ፡ ተው !

አሳብ ፤

አይ ፡ ጥጋብ ፡ ይለዋል ፡ እሱ ፡ ስለበላ !
ሁሉም ፡ እንዲበላ ፡ እንደመፍጠር ፡ መላ ፤
መላ ፡ ብሎ ፡ ይዞት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቁጣ ፤
ከተመስገን ፡ በቀር ፡ ካፍህ ፡ እንዳይወጣ ፤
እያለ ፡ ሲዘልፈው ፡ ሃሞቱ ፡ ይፈሳል ።
የረሃቡን ፡ ቁጣ ፡ ችግሩን ፡ ይረሳል ።
« እቴ ፡ መላ ፡ ምቺ ፡ » እያለ ፡ ይዘፍናል ፡ መላውን ፡
ሳያውቀው !
ዘፉኙ ፡ የሚያስበው ፣
ቁም ፡ ነገር ፡ የሚለው ፡
ሌላ ፡ መቼ ፡ ሆነ ፡ ማወራረዱን ፡ ነው ።

እንደልቡ ፤

አንተ ፡ አዋቂ ፡ መሳይ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፍራ !
፣ጥንቱን ፡ ባሕላችን ፡ አስተውለህ ፡ አውራ ፤
ፉት ፡ ቢሉት ፡ ጭልጥ ፡
ምነው ፡ ተክለፈለፍክ ?
ያንተ ፡ ያልሆነውን ፡ ለማግኘት ፡ ሞከርክ !



መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡
የደጐቹ ፡ ቤት ፡ ናት ፤
የዘለዓለም ፡ ረፍት ፡ የሚያገኙባት ።


የጻድቁ ፡ ኢዮብ ፡ መከራና ፡ ሥቃይ ፡
በምድር ፡ አለፈ ፤
በዳቢሎስ ፡ ምክር ፡ አምላክን ፡ አማርሮ ፡ ስላልለፈ
ለፈ ።
ሲሰቃይ ፡ ኖሮ ፡ በኋላ ፡ አለፈለት !
መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ዛሬ ፡ የሱ ፡ ቤት ፡ ናት ።

በእውነቱ ፤

የምድሩን ፡ ሲሳይ ፡ ለሀብታሞች ፡ ሰጠ !
መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ በድሆች ፡ አጌጠ !
ሀብታም ፡ ተኰንኖ ፡ ደኃው ፡ ግን ፡ ይጸድቃል ፣
ድልድሉ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ የምትል ፡ ይመስላል ።
ለውጥ ፡ ቢያደርግም ፡ አምላክ ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፤
ደሀው ፡ ለደስታ ፡ ጌታው ፡ ለድኅነት ፤
መጽናኛ ፡ አይሆነውም ፤ ስቃዩን ፡ አስታግሶ ፤
የዛሬው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የነገው ፡ መች ፡ ብሶ !

የቃጠሎው ፡ ብዛት ! የእሳቱ ፡ ረመጥ ! ብሎ ፡ እያገነነ፡
ደኃ ፡ ሞኝ ፡ ነውና ፡ ነግ ፡ ይደርሳል ፡ ብሎ ፡ በአሳብ ፡
መነመነ ።
ልብላ ፡ ሲል ፡ እያጣ ፡ ልልበስ ፡ ሲል ፡ እያጣ ፤
ከዚህም ፡ ከባሰ ፡ የገሃነም ፡ ቁጣ !

ይህ ፡ ነው ፡ ስቃይ ፡ ማለት ፡ ተስፋን ፡ የሚያስቆርጥ ፤
ሆድን ፡ የሚያባባ ፡ የሚያንቀጠቅጥ ። »



በእውነቱ ፤

እኔ ፡ እንደሚመስለኝ ፡ ብቻውን ፡ አልወጣም ፤
ምሥጢር ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ተከታይ ፡ አላጣም ።



ታሪኩ ፤

በል ፡ ወንድሜ ፡ ተወን ፡ በጣም ፡ አደከምከን ፤
እንዳሻህ ፡ አድርገው ፡ መቼስ ፡ ካልሰማኸን ፤
እንለየዋለን ፡ አምላክ ፡ ይርዳህ ፡ ብለን ።

ኤፍሬም ፤

ምነው ፡ ግራ ፡ ገባኝ ፡ ምነው ፡ ተበጠበጥኩ !
የምመርጠው ፡ አጣሁ ፡ በከንቱ ፡ ተቸገርኩ ።
አሳቤ ፡ መጭ ፡ ይላል ፡ ግራ ፡ ቀኝ ፡ እያለ ፡ አትርፎ ፡
ላይመጣ ፤
ትርጉሙን ፡ አጣሁት ፡ ወይኔ ፡ የኔ ፡ ጣጣ ።

አሁንስ ፡ ይበቃል ፡ አንተ ፡ አሳብ ፡ ተለመን !
አመንምኖኝ ፡ ቀረ ፡ የኑሮ ፡ ሰቀቀን ።
መባከን ፡ በዛብኝ ፡ ከንቱ ፡ መዘላበድ ፡
የሚገላግለኝ ፡ ምነው ፡ አጣሁ ፡ ዘመድ ?

አሳብ ፤

አስቦ ፡ ለመኖር ፡ አስቦ ፡ ለመሥራት !
አግኝቶ ፡ ለመኩራት ፡ በልቶ ፡ ለመደሰት ፤
አልፈልግም ፡ ልራቅ ፡ ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ ጣጣ !
ሥርቼ ፡ አልበላም ፡ የመደሰት ፡ ኑሮ ፡ ካፍንጫዬ ፡
ይውጣ ፤
ባዮች ፡ በርክተዋል ፡ ድንቅ ፡ ነው ፡ ነገሩ ፤
ሊገባኝ ፡ አልቻለም ፡ ኃያል ፡ ነው ፡ ምስጢሩ ።

አየህ ፤

የሰው ፡ ልጅ ፡ ተፈጥሮ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ አይደል ፤
በመመኘት ፡ ብቻ ፡ ኑሮ ፡ አይደለል ፤
« እግዜር ፡ ያደርገዋል ፡ » እያሉ ፡ መጠበቅ ፡
ሳይሠሩ ፡ ቁጭ ፡ ብሎ ፡ በተስፋ ፡ መጨነቅ ፤
ካልተሠራ ፡ ውጤት ፡ አይገኝምና ፡ ሲዘገይ ፡ መሳቀቅ ፤

ተበላሽቶ ፡ ሲቀር ፡ እርስ ፡ በርስ ፡ መሳለቅ ።
አስብ ፡ እወቅ ! ሲሉት ፡ እምብየ ፡ አላውቅም !
ወይም ፡ ጠይቅ ፡ ሲሉት ፡ የለም ፡ አልጠይቅም ፤
ክፍሉ ፡ ከሰው ፡ ጋር ፡ ነው ፡ ልዩነት ፡ የለውም ።

ወይ ፡ጉድ !

ምርቱ ፡ ብዙ ፡ ነበር ፡ ቁም ፡ ነገሩ ፡ አነሰ ፤
እንክርዳዱ ፡ ሁሉ ፡ እየተቀነሰ ፤
ይሻሻላል ፡ ቢሉት ፡ እያደረ ፡ ባሰ ።
ዳቦን ፡ እንደመብላት ፡ ሊጥሙው ፡ የማይችል ፡ ከን
ፈሩን ፡ ነከሰ ።

ቢመከር ፡ ባሰበት ፡ ቢነገር ፡ ተቆጣ !
ሊገባው ፡ አልቻለም ፡ እምነትም ፡ ቢያጣ ።
አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ተመለስ ፡ ልበልው ፡
ካልሆነም ፡ ይቀራል ፡ ዘፋኞች ፡ እንዳሉት ፡ ነገሩ ፡
ያው ! ያው ፡ ነው ።
አይፈረድበት ፡ መቼም ፡ ተይዞ ፡ ነው ፤
ጊዜውን ፡ ለመምሰል ፡ ያቀደው ፡ ዘዴ ፡ ነው ።

ኤፍሬም ፤

የገዛ ፡ አከላቴን ፡ እየጠረጠርኩት ፤
ሁሉም ፡ በየተራ ፡ ባሳብ ፡ አናገርኩት ።

መጠርጠሬ ፡ አልቀረም ፤ ዓይኖቼ ፡ ቢያዩም ፤
ከፉንና ፡ ደጉን ፡ አጣርተው ፡ ቢለዩም ።

ጆሮቼም ፡ ቢሰሙ ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ አልኳቸው ።
ጊዜውን ፡ ለመምሰል ፡ እየረዳኋቸው ፤
መላሴም ፡ ቢናገር ፡ አትሳሳት ፡ አልኩት !
ሊያጠፉኝ ፡ ነበር ፡ እንደተረዳሁት ።

እናንተም ፡ እግሮቼ ፡ እርምጃችሁ ፡ ይጠር ፣
እንዳታጋልጡኝ ፡ በከዳችኝ ፡ ምድር ፤



እጆቼንም ፡ መከርኩ ፣
ጣቶቼን ፡ እያየሁ ፣
ትልቁ ፡ ትንሹ ፡
በግልጽ ፡ እየለየሁ ፣

ሌባ ፡ ጣቴ ፡ ነበር ፡ ጥቂት ፡ ያስቸገረኝ !
ያንንም ፡ ያንንም ፡ እያመለከተኝ ።

አውራ ፡ ጣቶቼማ ፡ እንዲሁ ፡ አውራ ፡ ናቸው !
አይመለከቱም ፡ እኔም ፡ ባሳያቸው ።
ረዥሙ ፡ ጣቴ ፡ የተንቀዋለለው ፣
ጉልህ ፡ መሰለ ፡ እንጂ ፡ ይዞታው ፡ ግን ፡ ያው ፡ ነው ።

ለጌጥ ፡ የተሠራው ፡ የቀለበት ፡ ጣቴ ፣
አማረልኝ ፡ ብዬ ፡ እሱ ፡ ላይ ፡ እምነቴ ፤
ትናንሽ ፡ ጣቶቼ ፡ እዳር ፡ ላይ ፡ ያሉቱ ፡
ካላበሩ ፡ በቀር ፡ጉልበታቸው ፡ ከንቱ ፤

ፀጉር ፡ ተሸካሚው ፡ ራሴን ፡ ባስበው ፡
ጌጡ ፡ ሲቀርበት ፡ መላ'ጣው ፡ እሱ ፡ ነው ።

በውስጡ ፡ ያለው ፡ ማር ፡ ለጥቅም ፡ አልዋለም ፤
ይህ ፡ ይሻላል ብሎ ፡ አላሰላሰለም ።

ጥርሶቼን ፡ ባስተውል ፡ ከሁሉም ፡ የባሱ !
ከንፈሮቼን ፡ ብቻ ፡ እየነካከሱ ፤
ዓይኖቼን ፡ አይመስሉ ፡ ምንም ፡ አያለቅሱ ።

ይንከተከታሉ ፡ በምንም ፡ በምኑ ፣
ችግር ፡ ላይ ፡ መሆኔን ፡ ቢያዩም ፡ አያምኑ ።
አፍንጫዬስ ፡ ይቅር ፡ ምንም ፡ አይታማ ፣
ሲያሸት ፡ ኖሮአል ፡ ችታ ፡ ከሆነማ ፤

ቅንድቤንም ፡ ቢሆን ፡ ምንም ፡ አልወቅሰውም ፤
የዓይኖቼ ፡ ዘበኛ ፡ መሆኑን ፡ አልክድም ።

ሆዴማ ፡ አይወቀስ ፡ ስንቱን ፡ ችሎልኛል !
ጊዜውን ፡ በትዕግሥት ፡ አሳልፎልኛል ፤
የአፍንጫየን ፡ ሽታ ፡ አመስግኖልኛል ፤
ትዕግሥተኛው ፡ ሆዴ ፡ ሁሉንም ፡ የቻለው ፡
« ይህን ፡ ያንን » ማለት ፡ ባለመልመዱ ፡ ነው ።

ባሁኑ ፡ ዕድሜዬ ፡ ላንጓው ፡ አልሻም ፤
የማያገኘውን ፡ ማስከጀል ፡ አያሻም ።

ድኀነትን ፡ አውራሽ ፡ እምብርቴ ፡ ነው ፡ ክፉ !
ከደሀ ፡ ተቆርጦ ፡ በኔ ፡ መለጠፉ ።
አሁን ፡ ሥሩን ፡ ሰዶ ፡ እኔን ፡ አስቸገረ ፤
ሊላቀቅ ፡ የማይችል ፡ የዘር ፡ ሆኖ ፡ ቀረ ።

ተወቃሹ ፡ ክፍል ፡ ሌላው ፡ የትኛው ፡ ነው ?
የደም ፡ ጋን ፡ መነሻ ፡ መሀሉ ፡ ልብ ፡ ነው ?
ትዕዛዝ ፡ አቀባዩ ፡ የአእምሮ ፡ ነርቭ ፡ ነው ?
ይህን ፡ አድርግ ፡ ሲባል ፡ ደንጋጩ ፡ ልብ ፡ ነው ?

ተወቃሹ ፡ ክፍል ፡ ሌላው ፡ የትኛው ፡ ነው ?
ሲያዩት ፡ የሚያለቅስ ፡ ተልፈስፋሹ ፡ ዓይን ፡ ነው ?
ሽንትን ፡ የሚያጣራው ፡ የሆድ ፡ ኩላሊት ፡ ነው ?
አየር ፡ የሚነፋው ፡ ታዛገፉ ፡ ሳምባ ፡ ነው ?

ተወቃሹ ፡ ታዲያ ፡ የትኛው ፡ ክፍል ፡ ነው ?
እንደኔ ፡ ከሆነስ ፡ ሁሉም ፡ ተወቃሽ ፡ ነው !
አንዱ ፡ አንዱን ፡ ይዞ ፡ በድምር ፡ አልቃሽ ፡ ነው ።





ኤፍሬም ፤

ያመጣውን ፡ ይዞ ፡ እዩት ፡ አመለጠ !
ከቶም ፡ ላይጠረቃ ፡ ሄደ ፡ ፈረጠጠ ።
ይዞ ፡ ሲያመጣ ፡ ፈገግታን ፡ ያሳያል ፤
አብኖ ፡ ሲያሸሽ ፡ መልኩን ፡ ይለውጣል !
መጠየቅ ፡ አይወድም ፡ በቅድሚያ ፡ ይቆጣል !
ከጠቅላላው ፡ ዓለም ፡ ራሱን ፡ ይመርጣል ።

በእውነቱ ፤

ለችግርህ ፡ መፍትሔ ፡ ለስቃይህ ፡ መላ ፡
ራስህን ፡ ነዝንዝ ፤
ሐሞትህ ፡ አይፍሰስ ፡ አስብ ፡ አትደንዝዝ ፤

ሞክር ፡ ሁሉም ፡ ነገር ፡ አትዶልት ፡ ወሬ ፤
ለነገ ፡ በማሰብ ፡ አትቸገር ፡ ዛሬ ፤
ጠልቀህ ፡ አሰላስል ፡ ሆድህ ፡ አይሸበር ፡
አይሁንብህ ፡ ጥሬ ።

የዚህ ፡ ዓለም ፡ ኑሮህ ፡ አንዴ ፡ ተወስኗል ፤
ያለቀኑ ፡ አትሞተም ፤
ብትርመጠመጥም ፤
ስለተቸገርኸም ፡ ከቀኑ ፡ አታልፍም ።

ሐሞትህ ፡ አይፍሰስ !
እንዲሁ ፡ አትልፈስፈስ ፡ አደራህን ፡ ጠብቅ ፤
በሥጋ ፡ መንምነህ ፡ ነፍስህ ፡ አይጨነቅ ።
መኖር ፡ የማይችል ፡ ሰው ፡ መወለዱ ፡ አይበቃም !
ዕበት ፡ ትል ፡ መፍጠሩን ፡ ማስረዳት ፡ አያሻም ።

በፍቅር ፡ መጸነስ ፡ የሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ሕግ ፤
ዘጠኝ ፡ ወር ፡ መረገዝ ፡ የሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ሕግ ፤
ሰው ፡ ሆኖ ፡ መወለድ ፡ የሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ሕግ ፤
የኋላ ፡ ኑሮው ፡ ግን ፡ ለደካማው ፡ ወገን ፡ አይ ፡ ሲያስ
በረግግ !

በዕድል ፡ አመሃኙ ፡ ሰነፉ ፡ ተላሌ !
በሆዱ ፡ ተገገዞ ፡ የመኳንንት ፡ ሎሌ ፤
በቀኝ ፡ ጆሮህ ፡ ሰምተህ ፡ በግራ ፡ ባታፈስ ፤
አንዴ ፡ ብትፈነቅል ፡ ወኔህ ፡ ቢቀሰቀስ !!!



መሣይ ፤

ያንተ ፡ ተቀስቅሶ ፡ ምን ፡ ሲሠራ ፡ ታየ ?
የራስህ ፡ ሁናቴ ፡ መቼ ፡ መልኩን ፡ ለየ ?
በንግግር ፡ ብቻ ፡ ዋጋ ፡ ቢገኝማ ፤
የተወራው ፡ ሁሉ ፡ ተረት ፡ ባይሆንማ ፤
እስካሁን ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ተወርቶ ፡ ነበረ !
ጥቅም ፡ ግን ፡ የለውም ፡ ተዘርዝሮ ፡ ቀረ ።
ልተንፍስ ፡ በማለት ፡ ላመል ፡ ስለሚተች ፤
መካሪ ፡ ነኝ ፡ ይላል ፡ ለሀገር ፡ የሚመች ።
ላለንበት ፡ ዓለም ፡ የኑሮ ፡ እንቅፋት ፤
ወሬው ፡ ሲቀድም ፡ ነው ፡ ከዕቅዱ ፡ በፊት ።
ቢታሰብ ! ቢታሰብ ! በቁና ፡ አይለካ ፤
ስላሰቡ ፡ ብቻ ፡ ኑሮ ፡ አይሳካ ።

ኤፍሬም ፤

ምን ፡ አለ ፡ ልሞክር ፡ የሚሻል ፡ ከሆነ !
ከጭንቅ ፡ መቼ ፡ ወጣሁ ፡ ድሮስ ፡ እንደሆነ ።
የእኔ ፡ አስተሳሰብ ፡ ለእንጀራ ፡ ለቂጣ ፤
ከዚህ ፡ ለበለጠው ፡ ፊቴም ፡ አይቆጣ ፤
በዚህ ፡ ከረዳኸኝ ፡ ሆዴን ፡ ከዳኘኸው ፡
የመንፈሴን ፡ መቁሰል ፡ ለኔው ፡ ብቻ ፡ ተወው ።

ታሪኩ ፤

ሰማህ ፡ አቶ ፡ በእውነቱ !
እየከፉ ፡ ሄደ ፡ ኤፍሬም ፡ ተቸገረ ፤
በኃሳብ ፡ ምክንያት ፡ በጣም ፡ ተማረረ ።
ምንም ፡ ሳያርፍ ፡ ያድራል ፡ በመገለባበጥ ፡
ሲባንን ፡ ይታያል ፡ በጣም ፡ ሲቀበጠበጥ ።
ምነው ፡ ተው ፡ ብትለው ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብለህ ፤
አሁን ፡ ይኸ ፡ ደሀ ፡ ምን ፡ ይሁን ፡ ትላለህ ?

በእውነቱ ፤

የዚህ ፡ ዓለም ፡ ነገር ፡ በጣም ፡ ያስቸገረው ፤
ለፍጥረት ፡ መሻሻል ፡ እንቅፋት ፡ የሆነው ፤
ለሰው ፡ የማያስብ ፤ ራሱን ፡ የሚወድ ፡ በርከት ፡ ስላለ ፡
ነው ።

ለማን ፡ ብለህ ፡ ይሆን ፡ ታጥቀህ ፡ የመጣኸው ?
አዎ ? ግራ ፡ ቀኝ ፡ በማለት ፡ ጥቅምን ፡ ፍለጋ ፡ ነው ።

ሰማህ ! ለጥቅሙ ፡ ካልሆነ ፡ ለሰው ፡ ደግ ፡ የሠራ ፡
ወይም ፡ የተመኘ ፡
እውነተኛ ፡ ዳኛ ፡ መቸ ፡ በብዛት ፡ ተገኘ ?

እንዳንተ ፡ መሳዩ ፡ ራሱን ፡ የሚወድ ፤
እየፈጣጠረ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መንገድ ፤
ለድሎቱ ፡ ብቻ ፡ ዘወትር ፡ የሚጥር ፤
የሰውን ፡ እጅ ፡ አይቶ ፡ በልቶ ፡ የሚያድር ፤
እየበዛ ፡ ሄደ ፡ ቁጥሩ ፡ በረከተ ፤
ማሰብን ፡ በመጥላት ፡ ቁም ፡ ነገርን ፡ ሳተ ።

ሰማህ ፡ ኤፍሬም !

እወቅ ፡ አለህ ፡ እንጂ ፡ አሳብ ፡ መቼ ፡ ጎዳህ !
ተኝቼ ፡ በሕልሜ ፡ መጣብኝ ፡ ትላለህ ፤
ለራስህ ፡ አታስብ ፡ ለሰው ፡ ትኖራለህ !
የሰነፎች ፡ ንብረት ፡ መጠቀሚያቸው ፡ ነህ ፤

አሳብ ፡ ሲደግፍህ ፡ አትሳሳት ፡ ብሎ ፤
ሰነፉም ፡ ይመጣል ፡ ከንፈሩን ፡ አሹሎ ፤
የተቁረቆረ ፡ ያዘነልህ ፡ መስሎ ።

መቼም ፡ ተነግሮሃል ፡ ቢገባህ ፡ ጥሩ ፡ ነው ፤
አንተን ፡ የመሰለ ፡ ሙሉ ፡ የሆነ ፡ ሰው !
ምን ፡ እንደሚበጀው ፡ ማወቅ ፡ ሲያቅተው !
በጤናው ፡ ነው ፡ ማለት ፡ አጠራጣሪ ፡ ነው ።



ለሥራ ፡ ፊት ፡ ሲሳይ ፡ ሆነህ ፡ እንዳትቀር ፡
አሁንም ፡ ብትነቃ ፡ መተኛትህ ፡ ቢቀር ።

ኤፍሬም ፤

አይ ፡ጉድ ! ይደንቃል !
በየተራ ፡ መጥተው ፡ አታስብ ፡ እያሉኝ ፤
ግጠው ፡ እንዲበሉኝ ፡ በዘዴ ፡ አሞኙኝ ።

አምላክ ፡ ነው ፡ አሳቢው ፡ ምንም ፡ አትጨነቅ !
ፈጥሮ ፡ አይተውህም ፡ ከአሳብ ፡ ተላቀቅ ፡
ብለው ፡ በመደለል ፡ ሲያጠቁኝ ፡ኖሩ ፤
ከቶም ፡ ሳልረዳው ፡ ሳላውቀው ፡ ምስጢሩ ።

አሁን ፡ ገለጽክልኝ ፡ እንዲያ ፡ ስትጨነቅ !
እንዲያ ፡ ስትጉላላ ፤
ለመጭው ፡ኑሮዬ ፡ ተገኘለት ፡ መላ ።

ምስጢሩ ፡ ሳይገባኝ ፡ በከንቱ ፡ ተሞኘሁ !
በቅማል ፡ በተባይ ፡ ተፍቄ ፡ ተበላሁ !
ሥጋዬ ፡ አለቀና ፡ አጥንቴም ፡ ተጋጠ ፡
ዘዴው ፡ በየጊዜው ፡ እየተለወጠ ።

ዘመቻ ፡ መሉ ፡ ዓለም ፤

መ . . . . ጭ ! !
አሳቤ ፡ እ . . ል , . ም ! አለ ፡
ጉ . . . ዞ . ውን ፡ ቀጠለ ፡
እ . . . ል . . . ም !

በእውነቱ ፤

ፍጥረት ፡ ካላሰበ ፡ ካላሰላሰለ ፤
ሰው ፡ መስሎ ፡ ካልታየ ፡ ከሰው ፡ ጋር ፡ ካልዋለ ፤
በየምክንያቱ ፡ ከተጨናነቀ ፤
ሰው ፡ ከሚያሰኘው ፡ ከኀሳብ ፡ ከራቀ ፤

እንስሳን ፡ ይመስላል ። በመልኩ ፡ ቢለይም ፡
ሰው ፡ እየተባለ ፡ ባለም ፡ ላይ ፡ ቢታይም ።

ተኝቶ ፡ በከንቱ ፡ ብስጭት ፡ አያሻም ፤
ካልሠሩ ፡ በስተቀር ፡ ኑሮ ፡ አይሟላም ።

አሳብ ፤

እንዲህ ፡ ነው ! ከተመለስክማ ፡ ልቦና ፡ ከሰጠህ ፤
የመኖርን ፡ ትርጉም ፡ አሁን ፡ ትረዳለህ ።
ከጠዋት ፡ ጀምረህ !
ቀውለል ፡ ስትል ፡ ውለህ ፡ ማታ ፡ ትገባና ! ቢኖር ፡
ትበላና !
ድሪቶህን ፡ ለብሰህ ፡ ጋደም ፡ ትልና !
በቅማል ፡ በትኋን ፡ አጥንትህ ፡ ይጋጣል ፤
መርጠህ ፡ አትለብስም ፡ ሠርተህ ፡ ካላተረፍክ ፡ ከወ
ዴት ፡ ይመጣል ?

አሁን ፡ ግን ፡ ተመስገን ፡ ነገሩ ፡ ገብቶሃል ፡
ለሥራ ፡ ከታጠቅህ ፡ አምላክ ፡ ይረዳሃል ፤
የሰውን ፡ እጅ ፡ ሳታይ ፡ በልተህ ፡ ትኖራለህ ፡
ለብሰህ ፡ ታጌጣለህ ፤
ከቁንጫ ፡ ስቃይ ፡ ትገላገላለህ ።

ኤፍሬም ፤

በቃ ፡ ቆርጫለሁ ! ነገሩ ፡ ገብቶኛል ፤
የቀድሞም ፡ ጥፋቴ ፡ አንጀቴን ፡ በልቶኛል ።

ካሁን ፡ ወዲያ ፡ በቃኝ ፡ ከንቱ ፡ መበለጡ !
ጉድለቴ ፡ ኃያል ፡ ነው ፡ ገብቶኛል ፡ በቅጡ ።

ካልሠሩ ፡ ማግኘት !
ካልበሉ ፡ መጠርቃት !
ካልተቀበሉ ፡ መውዛት ፤



ምኞት ፡ ስለሆነ ፡ ጥቅሙ ፡ አይታይም ፤
ቀን ፡ እየተወራ ፡ በሕልም ፡ ቢታይም ።

ታሪኩ ፤

ኤፍሬምን ፡ ለወጠው ፡ ይህ ፡ ክፉ ፡ ሰባኪ !
እየደረደረ ፡ የአሰት ፡ ትርኪ ፡ ምርኪ ፤
መሐረነ ፡ ክርስቶስ ፡ አምላክ ፡ ተለመነን !
ከችግር ፡ አድነን ፡ በሰላም ፡ አኑረን ።

ኤፍሬም ፤

እናንተን ፡ አምኜ ፡ ሁሉንም ፡ ጠረጠርኩ !
ለኔ ፡ የማይበጀኝ ፡ ጠላቴ ፡ ነው ፡ እያልኩ ፤
አሳብን ፡ በመሸሽ ፡ እስህተት ፡ ላይ ፡ ወደቅኩ ።

አሁን ፡ ግን ፡ አያሻም ፡ መበለጥ ፡ ይበቃል !
ከአሳብ ፡ ልለይ ፡ ማለት ፡ ከመስመር ፡ ያወጣል ።
ማሰብ ፡ የሚጎዳኝ ፡ መስሎኝ ፡ እኖር ፡ ነበር ፡
ነገር ፡ ግን ፡ አይደለም ፤
ካለማወቅ ፡ ሌላ ፡ የሰው ፡ ጠላት ፡ የለም ።

ሰዎች ፡ ይባላሉ ፡ ሰነፎች ፡ በሙሉ ፤
ግራ ፡ ቀኝ ፡ እያሉ ፡ እያውደለደሉ ።
እኔንም ፡ ጐተቱኝ ፤
አታስብ ፡ እያሉኝ ፤
የሥራ ፡ ጊዜዬ ፡ በወሬ ፡ አስጣሉኝ ።
እድሜዬ ፡ አዘገመ ፡ ምንም ፡ ሳልሠራበት ፤
አንጐሌ ፡ አይበቀል ፡ ጊዜ ፡ አለፈበት ፤

ዕድሜ ፡ አይመለስ ፡ እንደጐርፍ ፡ ይጠፋል !
ምንም ፡ ሳይታወቅ ፡ ሸርተት ፡ ብሎ ፡ ያልፋል ።

ሊጨበጥ ፡ አይችልም ፡ በኋላ ፡ ቢሮጡ !
ያለንበት ፡ ዓለም ፡ ልጅነት ፡ ነው ፡ ጌጡ ።

ይህ ፡ ሁሉ ፡ ቢገባኝ ፡ ባሁኑ ፡ እድሜዬ ፤
ከመቆጨት ፡ በቀር ፡ ሊጠቅመኝ ፡ አይችልም ፡ አለቀ፡
ጊዜዬ ።
የሰውን ፡ እጅ ፡ አይቶ ፡ መኖር ፡ ብቻ ፡ ቀረኝ ፤
ከልመና ፡ ኑሮ ፡ አቤቱ ፡ ገላግለኝ ።

በእውነቱ ፤

ምን ፡ ያደርጋልሃል ፡ ላለፈው ፡ ብታለቅስ ?
ከቶም ፡ ላታገኘው !
ለመጭው ፡ ማሰብ ፡ ነው ፡ ያለፈውን ፡ ተወው ።
አምላክ ፡ ነው ፡ አሳቢው ፡ የሚለውን ፡ ይዘህ !
በመጾለት ፡ ብቻ ፡ ያለፍሬ ፡ ቀረህ ።

ዕድሜህ ፡ ገፋ ፡ ብሏል ፡ ሐሰት ፡ አይባልም ፤
ከእንግዲህ ፡ ሩጠህ ፡ ብዙ ፡ አታተርፍም ፤
ዕድሜ ፡ አይመለስ ፡ መድኃኒት ፡ የለውም ።
ዳሩ ፡ ግን ፡ ቢሆንም ፡ ባለህ ፡ ቀሪ ፡ ጊዜ ፡ ጀምረህ ፡
ካሁኑ !
ከሥራ ፡ በስተቀር ፡ አንጎልህ ፡ አይያዝ ፡ በምንም ፡
በምኑ ፤

ሰማህ !

ጐርፍ ፡ የወሰደውን ፡ ጐርፍ ፡ አይመልሰውም ፡
ያሁኑ ፡ ቂጭትህ ፡ ጊዜ ፡ አልፎበታል ፡ ትርጉምም ፡
የለውም ።
ላገርህ ፡ ልፋለት ፡ እንዲሁም ፡ ለግልህ ፡
ይኸው ፡ ነው ፡ ይበቃል ፡ እግዚአብሔር ፡ ይርዳህ ።

ዘመቻ ፡ ሙሉ ፡ ዓለም ፡


መ ! ! ! ! ! ጭ ! ! ! !
ጭ ! ! ! ! ! ! ል ! ! ! ! ! ! ! ! ! ! ! ! ! እልም ! !

(መጋረጃ) ፤ (፬ኛ ፡ ትርኢት)



(ዘመቻ ፡ ሙሉ ፡ ዓለም ፡ ኤፍሬም ፡ አሳብ ፡ ታሪኩና ፡
መሳይ ፡ አብረው ፡ ይቀመጣሉ ። )
ዘመቻ ፡ ሙሉ ፡ አለም ፡

መ ! ጭ ! ጭ ! ! ! ! !
እ ! ! ! ! ል ! ! ም ! ! ተነሳሁኝ !
ገንዘብ ፡ ሳላወጣ ፡ ቲኬት ፡ አገኘሁኝ ፤
ይሄ ፡ ነው ፡ ! ! !
አሳብ ፡ ቀልቤ ፡ ነው ፡ ምን ፡ ምግብ ፡ ያሻኛል !
መ ! ! ! ጭ ! ! ል ! ! ጥ ! ! ደከምኩ ፡ ይበ
ቃኛል ።
ሰላም ፡ አጥቻለሁ ፡ እንዲሁም ፡ ጸጥታ !
መንፈሴ ፡ ታወከ ፡ ሥጋዬም ፡ አለቀ ፡ አድምጡኝ ፡
በርጋታ ።
ብ ! ! ው ! ! ይኸው ፡ መጣ ! አቤት ፡ ስዞር !
አቤት ፡ ስንቀዋለል !
እዩኝ ፡ ተመልከቱኝ ፡ ካሳብ ፡ ጋር ፡ ስታገል ።



መ----ጣ----ሁ !



ብ ! ! ብ ! ! ው ! እልም ፡ አልፈልግም ፡ ልጥፋ ! ከንቱ፡
ለምን ፡ ልልፋ ?

ሥጋዬ ፡ ተኝቶ ! አሳቤ ፡ እልም ፡ አለ ፡ በረርኩኝ ፡
ባየር ፡ ላይ !
በቃኝ ፡ አልመኝም ፡ የምድሩን ፡ሲሳይ ።

እ ! ል ! ም ፡ ያውላችሁ ፡ ብክንክን ፡ ብያለሁ ፡
ለዚህ ፡ ዓለም ፡ ኑሮ ፡ እርሜን ፡ አውጥቻለሁ !

ባሕር ፡ ሳያስፈልግ ፡ ባየር ፡ ላይ ፡ መዋኘት !
ድንበር ፡ አለፍክ ፡ ተብሎ ፡ ጭቅጭቅ ፡ የለበት ።

በሮ ፡ መመለስ ፡ ነው ፡ መቼ ፡ በግር ፡ መሄድ ፡
ምንም ፡ ጊዜ ፡ አይወስድ ፡ ፍጥነቱ ፡ በሴኮንድ !

መቀመጥ ፡ በፎቴ ፡ በማይቆረቁረው !
እድሜ ፡ ለምኞቴ ፡ ሳልሠራ ፡ መብላት ፡ ነው ።

ጭልጥ ፡ ! ! ! በየስፍራው ፡ በቃ ፡ አልመለስም !
እዚያው ፡ ይሻለኛል ፤
መጐለት ፡ መቀመጥ ፡ በጣም ፡ ሰልችቶኛል ።

ፍዋ ! ! ፍዋ ! ! ባየር ፡ በረርኩ ፡ ተሰናበትኳችሁ ፡
ዕድሜ ፡ ለምኞቴ !
ተመስገን ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ሞላ ፡ ፍላጐቴ ።
ጉድ ፡ ነው ! !

የዚህ ፡ ዓለም ፡ ኑሮ ፡ ውዝግቡ ፡ ብዙ ፡
አሳብ ! ስቃይ ! ረሃብ ! ችግር ! አቤት ፡ አበዛዙ !


ጣጣው ፡ መበርከቱ ፡ ኧረ ፡ ለምንድር ፡ ነው ?
ነገ ፡ ሞት ፡ እያለ ፡ ዋዜማው ፡ ለምን ፡ ነው ?

አሳብ ፤

መቼስ ፡ ምን ፡ ይደረግ ፡ አንተም ፡ ተይዘሃል ፡
አዋቂዎች ፡ አንሰው ፡ ቂላ ፡ ቂሉ ፡ በዝቶአል ።

ጓደኛህ ፡ ያውልህ ፡ አብራችሁ ፡ ታጎሩ ፤
ምንም ፡ ሳታስቡ ፡ ለመኖር ፡ ሞክሩ ።
በናንተ ፡ ዘንድ ፡ እኮ ፡ ማሰብ ፡ ነው ፡ ችግሩ !





ኤፍሬም ፤

ወንዱ ፡ ቢያገለድም ፡ ቁርጤን ፡ አውቀው ፡ ነበር ፤
አሁን ፡ የቸገረኝ ፡ የወንዶቹ ፡ ነገር ።

አብርሮ ፡ ሲጠፋ ፤
የሚናገር ፡ እንጂ ፡ አስታዋይ ፡ መች ፡ ጠፋ ።

ዘመቻ ፡ ሙሉዓለም ፡

እግዚአብሔር ፡ አለልን ፡ አንተ ፡ ብቻ ፡ ተወን !
ከኛ ፡ ጋር ፡ ተጣብቀህ ፡ ምንም ፡ አልጠቀምከን ።

እንዳፈጣጠሬ ፡ ቀስ ፡ ብዬ ፡ ስራመድ ፤
የምን ፡ ልዩ ፡ ልማድ ? የምን ፡ ልዩ ፡ መንገድ ?

ምድር ፡ እሳት ፡ ቢነድ ፡ ሰማይን ፡ አይፈጅም ፡
ሌላው ፡ የሰራውን ፡ መከጀል ፡ አይበጅም !

አሳብ ፤

ጊዜ ፡ የወለዳቸው ፡ ጥርቅምቅሞች ፡ ሁሉ ፡
ምነው ፡ ያለ ፡ ገመድ ፡ የትም ፡ ይሳባሉ ?

ዘመቻ ፡ ሙሉ ፡ ዓለም ፤

ኧረ ፡ በምን ፡ ዓይነት ፡ አሳቤን ፡ ልግለጸው ?
አምላክ ፡ የፈጠረን ፡ ሊረዳንኮ ፡ ነው ፤
የእለት ፡ እንጀራችን ፡ ስጠን ፡ የምንለው !
ኪርያ ፡ ላይሶን ፡ እያልን ፡ ጠዋትና ፡ ማታ ፡
የምንጸልየው !
እንጀራን ፡ ካልሰጠን ፡ ታዲያ ፡ ለምኑ ፡ ነው ?

አሳብ ፤

አይ ፡ ጉድ ፡ ትገርማለህ ፡ የማይገባህ ፡ ድፍን !
እንዳንተ ፡ ያሉትን ፡ አግበስብሶ ፡ ማፈን ፤

ፍጥረት ፡ ቢበረክት ፡ ቁጥሩ ፡ ቢንዛዛ ፤
ቁም ፡ ነገር ፡ ሳይሠራ ፡ ረግፎ ፡ ከቀረ ፡ እንደ ፡ ጠዋት ፡
ጤዛ ፤
የሀገር ፡ ሸክም ፡ ነው !
ኑሮው ፡ መላ ፡ የለው !
በመወለዱ ፡ ግን ፡
ቁጥሩ ፡ ከሰው ፡ ጋር ፡ ነው ።



እሱም ፡ ሰው ፡ ነኝ ፡ ይላል ፤ መላሱን ፡ አሹሎ ፡
በወዲህ ፡ በማፍሰስ ፡ በዚያ ፡ ተቀብሎ ።

አምላክ ! አምላክ ፡ ብለህ ፡ ጸሎት ፡ ብታደርግም ፡
ኪርያ ፡ ላይሶን ፡ ብትል !
ስትጮህ ፡ ብትውል !
ካልሠራህ ፡ በተቀር ፡ ምንም ፡ አይረዳህም ።

እኔን ፡ ይብላኝ ፡ ይላል ፡ አልቃሽ ፡ ሳይቸግረው ፤
ጭራሽ ፡ ላላወቀው ፡ ዘመዱ ፡ ላልሆነው ፤
ከሥራ ፡ ለመራቅ ፡ ያቀደው ፡ ዘዴ ፡ ነው ።

ዘ. ሙ . ዓ ፤

በፉካሬ ፡ ኢየሱስ ፡ የተወራው ፡ ሁሉ ፡
ሲከበር ፡ የኖረው ፡ ሥርዓቱ ፡ ባህሉ ፤
ሰለጠንን ፡ ባዮች ፡ ሊሽሩት ፡ ነው ፡ አሉ ፤
ገደል ፡ ሊሰዱት ፡ ነው ፡ ሰዎች ፡ ቻል ፡ አትበሉ !

« እመኑት ፡ ለምኑት ፡ አቤት ! አቤት ! በሉት ፤
ኑሩ ፡ በተጋድሎ ፡ በጾምና ፡ ጸሎት !
እንዲሰውራችሁ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ክፋት » ፤
ብሎ ፡ ሲያስጠና ፡ ሲያስተምር ፡ ኑሮ !
እንደዚያው ፡ እያለ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ተፈጥሮ ፤

ምነው ፡ ተንጠራራ ፡ ድፍረትን ፡ አበዛ ?
የእግዚአብሔር ፡ ምስጢር ፡ ላይገኝ ፡ በዋዛ !

አምላክ ፡ የሚሳነው ፡ የማይችል ፡ ይመስል !
በተንኮል ፡ ተመርቶ ፡ ደካማን ፡ ማስመሰል ፤
ይልቅስ ፡ አምላክን ፡ ይቅር ፡ በለኝ ፡ በለው ፡
ከመስመር ፡ አትውጣ ፡ መደለሉን ፡ ተወው ።

አሳብ ፤

አንተን ፡ ትቼሃለሁ ፡ አልበሰልክምና ፡
ማሰብ ፡ መመራመር ፡ መስሎሃል ፡ ፈተና ።

ኤፍሬም ፤

አስብ ! አላስብም ! በሚለው ፡ ክርክር ፡ እስካሁን ፡
　　ቆይቼ ።
ምንም ፡ ሳላፈራ ፡ አእምሮዬ ፡ ዞረ ፡ በቁመና ፡ ሞቼ ፤
ከንፈሬን ፡ ብነክሰው ፡ አሁን ፡ ምን ፡ ያደርጋል !
የሌሎቹ ፡ እንጂ ፡ የኔ ፡ ሰዓት ፡ አልቆአል ።

እንዲያው ፡ በድን ፡ ሆኜ ፡ ያለፈውን ፡ ጊዜ ፡ መለስ ፡
ብዬ ፡ ሳየው ፤
እንዲሁ ፡ በእንዲሁ ፡ በከንቱ ፡ ሳለፈው ፡
በቁሜ ፡ ሞቻለሁ ፡ እየዬ ፡ ብቻ ፡ ነው ።
አዎ ! ኧረ ፡ አዎ !
ዋይ ! ዋይ ! ብሎ ፡ ማልቀስ ፡ እኔን ፡ ለመሰለው !
አንጀቱ ፡ ሳረረ ፡ በቁሙ ፡ ሳለው ፡ ነው ።

ዘ . ሙ . ዓ ፡

አይ ፡ ጉድ ! ለካስ ፡ ሞትም ፡ አለ !
እንዴ ! እንዴ !
ሰው ፡ ለምን ፡ ይሞታል ? የምን ፡ ጨዋታ ፡ ነው ?
ሳይፈልግ ፡ ተፈጥሮ ፡ ኋላ ፡ ዓለም ፡ ሲጥመው ?
በመሃል ፡ መጥፋቱ ፡ ትርጉሙ ፡ ምንድነው ?

እንዴ !

ወጥመዱን ፡ ያበጀው ፡ አምላክ ፡ ለምን ፡ ይሆን ?
አይመረመርም ፡ ሥልጣኑ ፡ እንደሆን !

ይግባኝ ፡ እንዳልሞት ! !

መፈጠሬ ፡ ደግ ፡ ነው ፡ በሞት ፡ ካልተቀጣሁ !
ሳልወድ ፡ በመገደድ ፡ ካለም ፡ ገጽ ፡ ካልጠፋሁ ።
ሁሉም ፡ በየተራው ፡ በየምክንያቱ ፤
በድንገት ፡ ይጠራል ፡ ያለ ፡ ፍላጎቱ ።



ባለም ፡ ጣዕም ፡ ስደሰት ፡ ድንገት ፡ ይመጣና !
ሲቀጨኝ ፡ ይታያል ፡ ሥልጣኑ ፡ ሆነና ፤
ሳላስብ ፡ በድንገት ፡ መኖሪያህን ፡ ለውጥ ?
በቃህ ፡ አትቀላውጥ !
ያለህበት ፡ ዓለም ፡
ለጉብኝት ፡ እንጂ ፡ መኖሪያህ ፡ አይደለም ፤
ብሎ ፡ ሲፈርድብኝ ፤
ምክንያት ፡ ሳይሰጠኝ !
መሬቷ ፡ ተከፍታ ፡ መልሳ ፡ ልትውጠኝ ።

በላቤ ፡ ለመብላት ፡ ገና ፡ ስፍጨረጨር ፡
ከተፍ ፡ ይልብኛል ፡ ውጥኔ ፡ እንዲቀር ።
ስሜ ፡ እንዲቀበር !
ዘመድ ፡ እንዲሸበር ፡
በኔም ፡ የሚረዳው ፡ ተጉላልቶ ፡ እንዲቀር ፤
በሞት ፡ ይቀጣኛል !
ሳልወድ ፡ ያጠፋኛል ።

የኔ ፡ ከዚህ ፡ መጥፋት ፡
ላትጠቀምበት ፤
ወይ ፡ ጨዋታ ፡ ሆኖ ፡ ላትደሰትበት ፤
በዚሁ ፡ ዓለም ፡ ልኑር ፡ ይግባኝ ፡ እንዳልሞት !

ማርያም ፡ አማልጅኝ ፡ ልኑር ፡ በዚህ ፡ ዓለም !
ሚካኤል ፡ አማልደኝ ፡ ልኑር ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡
ልታይ ፡ ለዘለዓለም !
ገብርኤልም ፡ አማልደኝ ፡ ፈጥነህ ፡ ድረስልኝ !
ሩፋኤልም ፡ ና ፡ ጭንቄን ፡ ተረዳልኝ !
ነቢያት ፡ ሰማዕታት ፡ ጌታን ፡ ለምኑልኝ ።

ጌታን ፡ ለምኑልኝ !
ድምጼን ፡ አሰሙልኝ !
ተፈጥሮ ፡ ከመጥፋት ፡ ከመሞት ፡ ያድነኝ ።

በየምክንያቱ ፡ መቀጨቴ ፡ ይቅር !
ልኑር ፡ በዚህ ፡ ዓለም !
ባላውቀው ፡ ነገር ፡ የሚደሰት ፡ የለም ።
አምላክ ፡ ተለመነኝ ፡
ሞትን ፡ አስቀርልኝ !
ኑሮየ ፡ አይወሰን ፡ ልኑር ፡ ፍቀድልኝ ።

ቢሻኝ ፡ ልንከራተት ፤

ግራ ፡ ቀኝ ፡ ልበል ፡ ባለም ፡ ላይ ፡ ልደሰት !
ወይም ፡ ደሀ ፡ ልሁን ፡ ቢሻኝ ፡ ልንከራተት ፤
እኔ ፡ መሥራት ፡ ባልችል ፡ የሌላን ፡ ልመልከት !
ላንተው ፡ አቤት ፡ ልበል ፡ ይግባኝ ፡ እንዳልሞት ።
እዚሁ ፡ ይሻለኛል ፡ ሌላው ፡ አያሻኝም !
ያለየሁት ፡ ዓለም ፡ አያስደስተኝም ፤
አዲስ ፡ ጎጆ ፡ ወጪ ፡ መሆን ፡ አያምረኝም ።

ልኑር ፡ ፍቀድልኝ !
ይግባኙን ፡ ስማልኝ ።
ውሳኔህን ፡ ለውጥ ፡ ሞትን ፡ አስቀርልኝ ።

አምላክ ! አንተ ፡ አምላክ ፡
ጥፋቴን ፡ አትመኝ ፡ ምን ፡ ያደርግልሃል ፡
ጠቃሚ ፡ ከሆነም ፡ ያለፈው ፡ ይበቃል ።

ኤፍሬም ፤

አይ ፡ ጉድ !
አስከሬኔን ፡ ማጌጥ ፡ ኋላ ፡ ለምንድር ፡ ነው ?
በሕይወት ፡ እያለሁ ፡ አበባየን ፡ ልየው ።
ሰሚው ፡ ግራ ፡ ገባው ፡ ዘመድም ፡ ሰለቸኝ ፤
የምለውን ፡ አጣሁ ፡ ጨነቀኝ ፡ ጠበበኝ ።
ኡ ! ኡ ! ብዬ ፡ ልጩሕ ፡ አንዴ ፡ እንኳን ፡ ላቅልጠው ፤
አያረካምና ፡ ቁጭት ፡ በደፈናው ።



እንጉሌ ፡ አይሠራም ፡ በቅቶታል ፡ ደከመ ።
አንጀቴም ፡ ደበነ ፤
ልቤም ፡ ተኝቶአል ፡ ሥራውን ፡ አቆመ ።

አደራ ፡ ልጆቼ ፡ በጣም ፡ ተጠንቀቁ !
ወሬን ፡ ከመዶለት ፡ ለሥራ ፡ ታጠቁ ፤
ፍሬአችሁ ፡ ታይቶ ፡ እንድትደነቁ ።

ያለሥራ ፡ ዋጋ ፡ ልባችሁ ፡ አይመኝ ፡
ምኞት ፡ አያደረጅ ፡ ብልጽግና ፡ አያስገኝ ።

ምክር ፡ ይሁናችሁ !
ቀልድ ፡ አይምሰላችሁ ! ያባታችሁ ፡ ችግር ፡
ሠርቶ ፡ ማፍራት ፡ ሲችል !
ዕድሜውን ፡ ለፈጀው ፡ ታሪኩ ፡ ሳያምር ።

አደራ ፡ በሰማይ ፡ አደራ ፡ በምድር ፡ በሥራችሁ ፡ ኩሩ
ለራሳችሁ ፡ እንጂ ፡ ለሰው ፡ አትኖሩ !
አንዴ ፡ ካመለጠ ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ ችግሩ !
የኔስ ፡ ነገር ፡ ቀረ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ተፈጥሮ ፡ ብዙ ፡
ነው ፡ ምስጢሩ ።

አሳብ ፤

ያሁኑ ፡ ኡ ! ኡ ! ታህ ፡ የሰው ፡ መሳቂያ !
ለተረት ፡ ይሆናል ፡ ጊዜን ፡ ማሳለፊያ ፤
እዩየህን ፡ ትተህ ፡ አሁንም ፡ በርትተህ ፡
ባለህ ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ መሯሯጥ ፡ አለብህ ።
የሚረዳ ፡ ቢሆን ፡ ጩኸትና ፡ ለቅሶ ፤
ሁሉም ፡ ለጥ ፡ ባለ ፡ እጁን ፡ አለስልሶ ።

ያለ ፡ ሥራ ፡ ዋጋ ፡ ማግኘትን ፡ መመኘት ፡
በልምምጥ ፡ ሆነ ፡ ወይ ፡ ደግሞ ፡ በጉልበት ፤
ከራስ ፡ ሊያልፍ ፡ አይችል ፡ ዋስትና ፡ የለውም !
ሊያኮራ ፡ አይችልም ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ አይቆይም ።

ኤፍሬም ፤

ተወኝ ፡ ይበቃኛል !
አሁን ፡ የምሰማው ፡ ምን ፡ ያደርግልኛል !
ጊዜው ፡ አልፎብኛል ፡ ጉልበቴ ፡ ከድቶኛል ፤
አበባው ፡ ጊዜዬ ፡ በከንቱ ፡ ጠውልጓል ።

ለእንቆቅልሽ ፡ ሁሉ ፡ ዋጋ ፡ እየሰጠሁ ፤
ሥራን ፡ ጠልቼ ፡ ኖርኩ ፡ ተጐልቼ ፡ ቀረሁ !

ዋጋዬ ፡ ብስጭት ፡ ትርፍ ፡ የሌለው ፡ ሆነ ፥
ልጅነት ፡ መልሶ ፡ የሚገኝ ፡ በሆነ ።
የልጅነት ፡ ጊዜዬ ፡ ሸርተት ፡ ብሎ ፡ አለፈ ፡ ምንም ፥
ሳልሰራበት !
ስመከር ፡ ስነገር ፡ እንዲያው ፡ ስወተወት ።

ቀኝ ፡ ጆሮዬ ፡ ሰምቶ ፡ በግራ ፡ ስልከው ፥
ምክሩን ፡ በመተርጎም ፡ በተንኮል ፡ ስወስደው ፥
ይተናነቀኛል ፡ ምን ፡ ብዬ ፡ ልግለጸው !
ያሁኑ ፡ ለቅሶዬ ፡ እንዲያው ፡ ለሰው ፡ ይምሰል ፤
ሠርቶ ፡ ፍሬን ፡ ያጣ ፡ አሳዛኝ ፡ ለመምሰል ።

እየሰረሰረ ፡ ከውስጥ ፡ ከሚያደብነኝ ፤
ኀዘኔ ፡ ተገልጾ ፡ ከውጭ ፡ በታየልኝ !

አዬ !

እየዬን ፡ ባበዛ ፡ እምባዬን ፡ ባጎርፈው ፡
ያለፈውን ፡ ጊዜ ፡ ከቶም ፡ ላልመልሰው ፡
በቁሜ ፡ ቅበሩኝ !
ዋይ ! ዋይ ! አትበሉ ፡ ዋጋዬ ፡ ይኸው ፡ ነው ።

አይሆንም ፡ ልሰቃይ ፡ እንባዬን ፡ ላፍሰው ፤
ፊቴ ፡ ይጨማደድ ፡ እንባው ፡ ይቦርቡረው !
እንባው ፡ በግልጽ ፡ ይታይ !



በሰውነቴ ፡ ላይ ፡ እንደጠበል ፡ ይረጭ ፡
ወይም ፡ ቀበራችሁኝ ፡ አዋቂ ፡ ይተካ ፡ በኔ ፡ ስፍራ ፡
ይፈንጭ !
በኔ ፡ ስፍራ ፡ ይፈንጭ !
ሠርቶ ፡ ጮማን ፡ ይብላ ፡ የማር ፡ ጠጅን ፡ ይጎንጭ ።

ዘ. ሙ. ዓ .

ደሀ ፡ የሞተ ፡ ዕለት ፡ « እሰይ ፡ እሰይ » በሉ ፥
ረፍቱ ፡ ነውና ፡ « ዋይ ፡ ዋይ » አትበሉ ፥
ዳሩ ፡ ማን ፡ ዋይ ፡ ይላል ፡ ለመናጢ ፡ ደሀ !
እንኳን ፡ ጠጅ ፡ ቀርቶ ፡ ላላጠጣ ፡ ውኃ ፤
ዳሩ ፡ ማን ፡ ዋይ ፡ ይላል ፡ ለራሱም ፡ ላልበቃ !
የኑሮን ፡ ጣዕም ፡ ሳያውቅ ፡ በቁም ፡ ለተጠቃ ፤
ዳሩ ፡ ማን ፡ ዋይ ፡ ይላል !
ደረቱን ፡ ይመታል !
ደሀው ፡ ስለሞተ ፡ ምኑ ፡ ተነክቶአል !
ዳሩ ፡ ማን ፡ ዋይ ፡ ይላል ፡ እኔን ፡ ይብላኝ ፡ ብሎ !
ከልመና ፡ በቀር ፡ እምን ፡ ሥራ ፡ ውሎ ?

ዳሩ ፡ ማን ፡ ዋይ ፡ ይላል ፡ ማንን ፡ ለማስለቀስ !
ጉዳቱ ፡ ሳይታይ ፡ በድፍን ፡ ለሚፈርስ !
ዳሩ ፡ ማን ፡ ዋይ ፡ ይላል ፡ ለየትኛው ፡ ውለታ !
አንዱንም ፡ ሳይሞክር ፡ በአሳብ ፡ ለተረታ ፤

ዳሩ ፡ ማን ፡ ዋይ ፡ ይላል ፡ ተዝካር ፡ ለማያበላ !
በሕይወቱ ፡ እንኳን ፡ ላልነበረው ፡ መላ ፤
ሲመኘው ፡ የነበር !
ረፍት ፡ አግኝቶአል ፤
ቀድሞ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ አሁንማ ፡ አርፎአል ።

ነፍሱን ፡ ይማር ፡ በሉ ፡ ሕይወቱስ ፡ አለፈ ፤
ሆዴን ! ሆዴን ! ብሎ ፡ እየለፈለፈ ።


ኤፍሬም ፤

አዬ ! በጣም ፡ የሚገርመኝ ! ሁለት ፡ ዓይንን ፡ ሰጥቶ ፡
ጆሮም ፡ ሰክቶልኝ !
የጅ ፡ ጣት ፡ የግር ፡ ጣት ፡ አፍንጫና ፡ ጸጉር ፡
ስላልጎደሉብኝ ፤
ሁሉም ፡ ተደምረው ፡ እኔን ፡ ሰው ፡ አሰኙኝ ፤
ይገርማል ፡ ይደንቃል ፡ ምነው ፡ ባያሞኙኝ !

ሞቶአል ፡ ይቀበር ፡ መባሉ ፡ አይቀርም ፤
በቁም ፡ መቀበሬን ፡ ሰው ፡ አልተረዳውም ።

ዘጠኝ ፡ ወር ፡ መረገዝ ፡ ተወልዶ ፡ ጡት ፡ ማለት ፤
ድሆ ፡ ተንከባልሎ ፡ ጉልበትን ፡ ማላመድ ፡
ግራ ፡ ቀኝ ፡ እያሉ ፡ ባለም ፡ ላይ ፡ መታየት ፤
ላዋቂዎች ፡ ኩራት ፡ ለሰነፍ ፡ ግን ፡ ሁከት ።





ኤፍሬም ፤

ትዕግሥቴ ፡ አለቀ ፡ ምነው ፡ ዝም ፡ አላችሁ ፤
በእናንተም ፡ የሚደርስ ፡ ከቶም ፡ አይመስላችሁ ።

አይዞህ ፡ ሲለኝ ፡ ኑሮ ፡ ሠርቶልኝ ፡ በነነ ፤
ለራሱ ፡ በመሥራት ፡ ስሙን ፡ አገነነ ።

በቃኝ ! ኧረ ፡ እስኪ ፡ በቃኝ !
መስታወቴን ፡ ልያዝ ፡ ፊቴን ፡ ልመልከተው !
አሁን ፡ ያለሁበት ፡ ሁናቴዬን ፡ ልየው ፤
ለነገሩ ፡ ያህል ፡ ግምቴን ፡ ልወቀው !
የሰው ፡ አፈጣጠር ፡ ነገሩ ፡ ረቂቅ ፡ ኑሮው ፡
ተያትር ፡ ነው ፤
ከጭቃ ፡ ተፈጥሮ ፡ ተመልሶ ፡ ያው ፡ ነው ፤
እውነት ፡ ከሆነማ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ነው ።

አይ ፡ ጉድ ! አይ ፡ ጉድ !
መሮጥ ፡ ሲያቅተኝ ፡ ሲደካክም ፡ ልቤ ፡
ሰውነቴ ፡ ሲያልቅ ፡ ጠፈፍ ፡ ሲል ፡ ላቤ ፤
ማታ ፡ ተገናኘን ፡ እኔና ፡ አሳቤ ፤

አሁን ፡ ይቅር ፡ በቃ ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ ሰለቸኝ !
መፍትሔው ፡ ቸገረኝ ፤
ያሳለፍኩት ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ህልም ፡ ታየኝ ፤

አጥንቴ ፡ ተዘጋጅ ፡ አሳቤን ፡ ተቀበል ፥
የሥጋዬን ፡ በደል ፡ ሥቃዩን ፡ ተበቀል ።
እንደምትረዳው ፡ ሥጋየስ ፡ አለቀ ፤
ለዚያቹ ፡ ኑሮዬ ፡ እየተጨነቀ ፤
ምላሴም ፡ ሲናገር ፡ እየተሳቀቀ ፤

ጆሮቼም ፡ ሲሰሙ ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ እያሉ ፤
ዓይኖቹም ፡ ሲያዩ ፡ እንባ ፡ እየሞሉ ፤
ከምራቅ ፡ በስተቀር ፡ ጥርሶቼም ፡ አልበሉ ።

አሳቤም ፡ ተዘጋጅ ፡ ተስማማ ፡ ካጥንቴ
ታውቀዋለህና ፡ የሥጋን ፡ ሁናቴ ።

መላሴ ፡ ተናገር ፡ አሁንስ ፡ አትፍራ ፤
አጥንት ፡ አይነካም ፤
ረቂቁም ፡ አሳብ ፡ በሕግ ፡ አይጠቃም ።



ሌላማ ፡ ምን ፡ ቀረኝ ፡ በርታልኝ ፡ የምለው ?
ካጥንትና ፡ ካሳብ ፡ የምደለድለው ?
ቁም ፡ ነገር ፡ የሌለው ፡ ሁሉም ፡ ተልፍስፋሽ ፡ ነው ።

ተኝቶ ፡ የኖረው ፡ የሻገተው ፡ አንጎል ፤
አሳብ ፡ ቢሞርደው ፡ ካጥንት ፡ ጋር ፡ ይደልደል ?
እንዴ ! ተወዝፎ ፡ ኖሮ ፡ እምን ፡ ሥራ ፡ ሊውል ?

የቈሰለው ፡ ነፍሴን ፡ ይቅር ፡ አልደልድለው !
የኋላ ፡ የኋላ ፡ አምላክ ፡ ይቀበለው ።

ኧረ ፡ ወዲያ ! ኀዘኔ ፡ ቢገለጽ ፡ ማንን ፡ ሊያሳዝን ?
የሥቃይ ፡ መጠን ፡ ከምን ፡ ሊመዛዘን ?
ቢቀርብኝሳ ! ይህ ፡ ሁሉ ፡ እሮሮ ፤
ተወርቶ ፡ አያልቅም ! ተነግሮ ፡ ተነግሮ ፤
ሊሳካም ፡ አልቻለም ፡ ተመክሮ ፡ ተመክሮ ።

ስለዚህ ፡ ይቅርብኝ ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ ሰለቸኝ ፥
መፍትሔው ፡ ቸገረኝ !
ያሳለፍኩትን ፡ ጭንቅ ፡ እንደሕልም ፡ ታየኝ ፤

በጥያቄ ፡ ልግታ ፡ ጽሑፌን ፡ ላሳጥር ፤
ለውጥ ፡ የሌለው ፡ ችግር ፡ ቢሰሙት ፡ አያምር ።
ኧረ ፡ ለመሆኑ !
ባለም ፡ ላይ ፡ ያለሁት ፡ በሕልሜ ፡ ? ? ? ?
? ? ? ? ? ? ? ? በውኔ ፡ ? ? ? ? ?
? ? ? ? ? ይህ ፡ ሁሉ ፡ እሮሮ ፡ ለጽድቅ !
? ? ? ? ? ? ? ? ? ? ? ለኩነኔ ! ! !
የወንድ ፡ ልጅ ፡ ያለህ ፡ እርዳታ ፡ አድርጉልኝ ፡
ለዚች ፡ ለድርሰቴ ፡ አርእስት ፡ ስጡልኝ ፤

<u>አርእስት ፡ ስጡልኝ</u> ።

# ፕሮብሌም ።

፩. የዓይኔ ፡ አበባ ፡ ባል ፡ ወደ ፡ ጦርነት ፡ እስከሄደበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ የነበረውን ፡ የቤተሰብ ፡ ሁናቴ ፡ ከ፴ ፡ መስመሮች ፡ ባልበለጠ ፡ ጽሑፍ ፡ በግጥም ፡ ግለጽ ።

፪. አቶ ፡ ወንድይፍራው ፡ ወደ ፡ ጦር ፡ ሜዳ ፡ ለመሄድ ፡ ከተነሳበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ የዓይኔ ፡ አበባ ፡ ኤፍሬምን ፡ ወደ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ እስከላከችበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ የነበራትን ፡ ችግር ፡ የሚገልጽ ፡ ፳፫ ፡ መስመር ፡ ግጥም ፡ ጻፍ ።

፫. ኤፍሬም ፡ የእናቱን ፡ ሕመም ፡ ሰምቶ ፡ « ሞታ ፡ ይሆን ፡ በሕይወት ፡ አገኛታለሁ ፡ » እያለ ፡ በመጨነቅ ፡ የሁለቱን ፡ ቀን ፡ የድንጋጤ ፡ ጉዞውና ፡ አጠገብዋ ፡ ቁጭ ፡ ብሎ፡ ሲላቀሱ ፡ የነበረውን ፡ ኀዘኑን ፡ የሚገልጽ ፡ በራስህ ፡ እንደ ደረሰ ፡ አድርገህ ፡ በ፴፫ ፡ መስመር ፡ በግጥም ፡ ጻፍ ።

፬. የኤፍሬምን ፡ ሁናቴ ፡ ባንድ ፡ ገጽ ፡ ተኩል ፡ ለሦስተኛ፡ ሰው ፡ አስረዳ ።

፭. ዘመቻ ፡ ሙሉ ፡ ዓለምና ፡ ኤፍሬም ፡ የሚመሳሰሉበት ፡ መንገድ ፡ እንዳለ ፡ ባጭር ፡ ግለጽ ።

፮. ኤፍሬም ፡ መጨረሻ ፡ በተቀበለው ፡ ምክር ፡ ተጠቅሞበታል ? አብራርተህ ፡ ጻፍ ።

፯. ኤፍሬምን ፡ ራሱን ፡ ከሚወድ ፡ ሰው ፡ ትመድበዋለህን ? ለምን ?

፰. ኤፍሬም ፡ በዜና ፡ ማርቆስ ፡ ገዳም ፡ ውስጥ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ፡ ከጭንቁ ፡ ፋታ ፡ ያገኘ ፡ መሆኑን ፡ ታሪኩ ፡ ይነግረናል ። የደስታው ፡ ምክንያት ፡ የነበረውም ፡ የማስተማር ፡ ሥራው እንደነበር ፡ ተወስቷል ። አባ ፡ ክንዴ ፡ የማስተማሩን ፡ ሥራ ፡ ያደናቀፉበት ፡ ምክንያት ፡ ለምንድነው ?